# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ እና የውሃ ሀብት አስተዳደር አፈጻጸም፣ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና እንደዚሁም ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ

## ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ማውጫ ........ 1

ማጠቃለያ (Executive summary):- ........ 3

ክፍል አንድ ........ 5

መግቢያ ........ 5

የባለሥልጣን መ/ቤቱ አመሰራረት ........ 6

የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ተግባርና ኃላፊነት ........ 7

የባለሥልጣኑ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል፡- ........ 9

የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ፡- ........ 9

የሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን የሥራ ፍሰት መግለጫ (process description) ........ 10

የኦዲቱ ዓላማ ፡- ........ 10

የኦዲት አካባቢ ........ 11

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች፡- ........ 11

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ - ........ 11

ክፍል ሁለት ........ 13

የኦዲቱ ግኝቶች ........ 13

ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ ስነ- ምህዳርን ከውድመት መከላከሉን በተመለከተ፡- ........ 13

በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ውስጥ የሚገኙ የተፋሰስ አካባቢዎች ጥበቃ በተመለከተ፡- ........ 16

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ሥራዎች ቀጣይነት እንዲኖረው መደረጉን በተመለከተ፡- ........ 20

ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀይቆች ላይ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮች የሚደርሱትን ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል የሚረዳ መመሪያ/ ማንዋል ማዘጋጀቱን በተመለከተ፡- ........ 22

በተፋሰሱ የውሃ አካላትን፣ ሐይቆቹንና የብዝሀ ሕይወቱን ሕልውና ከብክለት መከላከልን አስመልክቶ፡23

በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የአከባቢ ተጽኖ ግምገማን እና የግንዘቤ ሥራን በተመለከተ፡-........26

በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች ሥራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ስለመደረጉ፡-........27

የረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና የሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀምን በተመለከተ።........29

ባለሥልጣን መ/ቤቱ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-........31

በተፋሰሱ ውስጥ የሚካሄደውን ውሃ አጠቃቀምን መጠን እና ክፍያ እንዲሁም የፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ሥርዓት መዘረጋቱን በተመለከተ፡-........32

ባለሥልጣን መ/ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ ተፈጥሯዊ ሂደቱን ተከትሎ እየፈሰሰ ስለመሆኑ ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፡-........35

ባለሥልጣኑ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨት ለተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ያቀረበ ስለመሆኑ፡-........36

ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-........37

በተፋሰሱ ውስጥ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያስፈልጉ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች በቅንጅት መሰራታቸውን በተመለከተ፡-........38

በባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-........39

**ክፍል ሶስት**........42

***የመደምደሚያ ሃሳቦች***........42

**ክፍል አራት**........46

***የማሻሻያ ሃሳቦች***........46

**አባሪ 1: *የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን መዋቅር***........52

አባሪ- 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........................................................................ 53

አባሪ 3: በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸውአካላት እና መስክ ምልከታ የተደረገባቸው አከባቢዎች ዝርዝር ማሳያ፡- ........................................................................ 56

## ማጠቃለያ (Executive summary):-

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ እና የውሃ ሀብት አስተዳደር አፈጻጸም፣ ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና እንደዚሁም ውጤታማ መሆኑን በማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና መንስኤ በመለየት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ በሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለ ሥልጣን ላይ የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2009 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2006- 2008 ዓ.ም እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን በማካተት ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 ተዳፋትነታቸው ከ60 ፐርሰንት በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶች ለእርሻና ለልቅ ግጦሽ ለዛፍ፣ ለቋሚ ተክሎችና ለእንስሳት መኖ ልማት እንዲውሉ ቢደነግግም ተራራማ ቦታዎች የሚታረሱና ለልቅ ግጦሽ እየዋሉ ያሉበት ሁኔታ መኖሩ፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱ ድጋፍ የተሰሩ ስነ-አካላዊ ስራዎች የቴክኒካል ስታንዳርዱን ጠብቀው ያልተሰሩ እና የጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑ እንዲሁም የተሰሩ የስነ-አካላዊ (physical) ስራዎችን በስነ-ሕይወታዊ (Biological) ስራዎች አለመደገፋቸው፣
- ችግኝ ተከላ የተደረገባቸው ቦታዎች አጥር/ጥበቃ የሌላቸው መሆኑና አብዛኞቹ ያልጸደቁ መሆናቸው እና በባለስልጣኑ በጀት ድጋፍ የሚከናወኑ የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣
- በውሃ አካላቱ ላይ ፈቃድ ሳይወስዱ እና ሳያክሙ ወደ ሐይቆች የሚለቁ የልማት ድርጅቶችና ፋብሪካዎች መኖራቸው፣

- በሐይቆችና በረግረጋማ መሬቶች አካባቢ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት ላይ ክትትል በማደረግ በሚፈጠሩ ችግሮችና ጥሰቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረጉ፣
- በውሃ ተጠቃሚዎች መካከል የአጠቃቀም ግጭቶችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሮቹን ለመቅረፍ እና ፍትሃዊ የውሃ ሀብት አስተዳደር እንዲኖር ለማድረግ የሚስችል ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ለተለያዩ ሥራዎች ውሃን ለሚጠቀሙ አካላት በሙሉ ፈቃድ ያልሰጠ እና በፍቃዱ መሰረት ስለመስራታቸው የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- በውሃ ክፍያ ላይ የአከፋፈል ታሪፍ የሌለና፣ በተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ የውሃ ሀብት የሚጠቀሙ ድርጅቶች ለሚጠቀሙት ውሃ የሚከፍሉት ክፍያ የሌለ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ መደበኛ ሂደታቸውን እንዳይቀይሩ ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ የማያገኙ ከሆነ በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ የውሃ አካላት በደለል የሚሞሉ እና የሚበከሉ አልፎም ለበረሃነት በመገለጥ ሐይቆቹ እስከ መጥፋት ድረስ የሚደርሱ መሆኑን በኦዲቱ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የአፈርና ውሃ እንክብካቤ እና ጥበቃ ሥራዎችን በተፋሰሶቹ ውስጥ በስፋት በማከናወን ከባለድረሻ አካላት ጋር በመተባበር ዘላቂ እንዲሆኑ እና በተቀመጠላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በውሃ አካላቱ ላይ ፈቃድ ሳይወስዱ እና ሳያክሙ ወደ ሐይቆች የሚለቁ የልማት ድርጅቶችና ፋብሪካዎች ላይ ባለሥልጣኑ ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ በሁሉም የሀይቁ ዳርቻ (Buffer zone) ሊከለልና አስፈላጊው ጥበቃ እና እንክብካቤ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ በውሃ ተጠቃሚዎች መካከል የሚፈጠረውን ግጭት ለመፍታት እና ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ ውሃን ለሚጠቀሙ አካላት ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሊሰጥ፣ በየዓመቱ ፈቃዱን ሊያድስ እና በፍቃዱ መሰረት ስለመስራታቸው ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውሃን የሚጠቀሙ አካላትን በመለየት ለሚጠቀሙት ውሃ መጠን ክፍያ እንዲከፍሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ በመከታተል አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

  የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቁ የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ የ9600 ኪ.ሜ ርዝማን የሚሸፍንና ከቱርክ እስከ ሞዛምቢክ ተዘርግቶ የሚገኝ ነው፡፡ የምስራቅ አፍርካ ስምጥ ሸለቆ ደግሞ 6000 ኪ.ሜ ርዝማኔ ያለው ሲሆን በዉስጡ እሳተ-ገሞራዎችን፣ የተፈጥሮ ፍል ዉሀዎችን፣ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ እና ተፈጥሯቸው እጅግ ማራኪ የሆኑ ሐይቆችን በማካተት የያዘ ድንቅ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡
2. በኢትዩጵያ ይህ የስምጥ ሸለቆ የሚጀምረው በሰሜን ኢትዩጵያ በአፋር ክልል ደንከል ዝቅተኛ ቦታ ሲሆን እስከ ደቡብ ኢትዩጵያ ጫፍ የተለያዩ ሀይቆችን፣ ወንዞችን እና የተለያዩ የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ አካላትን ይዞ ይገኛል፡፡ ይህ የኢትዩጵያ ስምጥ ሸለቆ በተለይ እንደ ሰንሰለት የተያያዙ ሰባት ሀይቆችን የሚይዝ ሲሆን እነኝህ ሐይቆች የራሳቸው የሆነ የተለየ ባህሪ ያላቸው እና በውስጣቸውም የራሳቸው የሆነ የተለያዩ የብዝሀ ህይወት ሀብቶችን የያዙ በመሆናቸው እጅግ ውብና የቱሪስት መዳረሻ ጭምር ናቸው፡፡
3. የኢትዩጵያ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ሰባት ሐይቆችን ያካትታል፡፡ እነሱም የዝዋይ፣ የሻላ፣ አቢያታ፣ ላንጋኖ፣ ሀዋሳ እንዲሁም አባያና ጫሞ ሐይቆች ናቸው፡፡ ከነኝህ ሐይቆች ዝዋይ፣ አቢያታ፣ ሻላና ላንጋኖ በቅርብ ርቀት ተያይዘው በተፋሰሱ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኙ ሲሆን የሀዋሳ ሐይቅ በተወሰነ ርቀት በተፋሰሱ ማዕከላዊ ሲገኝ በተፋሰሱ ደቡባዊ ክፍል አባያና ጫሞ ይገኛሉ፡፡
4. የተፋሰሱ የቆዳ ስፋት 53,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስትና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ይገኛል፡፡
5. የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ በአራት ዋና ዋና ንዑስ ተፋሰሶች የተከፋፈለ ሲሆን እነርሱም፡-

1. ዝዋይ- ሻላ ንዑስ ተፋሰስ (14,477 ኪ.ሜ2)
2. ሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ (1,403 ኪ.ሜ2)
3. አባያና ጫሞ ንዑስ ተፋሰስና (18,118ኪ.ሜ2)
4. ጨው ባሕር ንዑስ ተፋሰስ (19,029ኪ.ሜ2) ናቸው፡፡

6. በተፋሰሱ 12.6 ሚሊዩን የሚሆኑ ህዝቦች የሚኖሩበት ሲሆን 13% በከተማ እና 87% በገጠር የሚኖሩ ህዝቦችን ሲይዝ ተፋሰሱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡-

7. በተፋሰሱ ባሉት የውሃ አካላት ውስጥ የሚገኘው የዓሳ ሀብት 70% የሀገሪቷን የአሳ አቅርቦት ሚሟላት እንደሚችል፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ ላይ ሚናው የማይናቅ መሆኑ፣ በፕሮቲን እጥረት ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችን ከመከላከል አንጻር የጎላ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፣

8. በተፋሰሱ 153,173 ሄክታር መሬት በመስኖ ሊለማ እንደሚችል መረጃዎች ያመለክታሉ፤ በተጨማሪም፡- የበርካታ የቤትና የዱር እንስሳቶች መኖርያ፣ የተለያየ ዝርያ ያላቸው ዓሳዎችና የውሀ ውስጥ እንስሶች መገኛ፣ከ500 በላይ የአእዋፍ ዝርያዎች መናሀሪያ፣ ከፍተኛ የጥናትና ምርምር ስራዎች የሚካሄዱበት እና ከፍተኛ የሆነ የቱሪስት ፍሰት የሚታይበት ተፋሰስ ነው፡፡

## የባለሥልጣን መ/ቤቱ አመሰራረት

9. በሀገራችን ኢትዮጵያ የሚገኙ የውሃ ሀብቶች የራሳቸው የሆነ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን ተከትለው የሚፈሱ በመሆናቸው ለቁጥጥር አመቺ እንዲሆን በማሰብ በተፋሰስ መከፋፈል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያ 12 ተፋሰሶች ያሏት ሲሆን እነዚህ ተፋሰሶችም በዓመት ወደ 123 ቢለዮን ሜትር ኪዩብ የገጸ ምድር ውሀ እና ከ30-40 ቢለዮን ሜትር ኪዩብ የሚሆን የከርሰ ምድር ውሀ እንደሚፈስ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

10. በሀገሪቱ ተፋሰሶች ውሰጥ ዘላቂ ልማትና አስተዳደር ማስፈን የተፋሰሶችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል አይነተኛ ስልት በመሆኑ በሀገሪቱ ባሉት 12 ተፋሰሶች የውሀ ሀብቱን በአግባቡ ለማልማትና ለመጠበቅ የተፋሰስ ባለስልጣን መ/ቤቶችን የማቋቋም ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ አገሪቱ ያላትን የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር ውሃን ታሳቢ በማድረግ ውሃ ትልቁ የሀገሪቷ ሃብት መሆኑ ስለታመነበት ባለስልጣኑ በ1987 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 4/87 ዓ.ም የውሃ ሃብት ሚኒስቴር በመባል በሚኒስቴር መስሪያ ቤት

ደረጃ የተቋቋመ ሲሆን፣ የአዋሽ ተፋሰስ የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለስልጣን እና የአባይ ተፋሰስ የውሃ ሀብት አስተዳደር ባለስልጣን እንደቅደም ተከተላቸው በአዋጅ ቁጥር 129/1991 እና ደንብ ቁጥር 151/2000 ዓ.ም ተጠሪነታቸው ለውሃ ሀብት ሚኒስቴር በመሆን ተቋቋመዋል፡

11. በተጨማሪ የተፋሰሶችን ባለስልጣናት በበላይነት የሚቆጣጣር የተፋሰስ ምክር ቤቶችና ባለስልጣናት በአዋጅ ቁጥር 534/1999 ዓ.ም ተቋቋሟል፡፡ ሲቋቋሙ የተቀናጀ የውሃ አስተዳደር ሂደት ፍትሃዊ እና አሳታፊ በሆነ መንገድ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ ተግራዊ እንዲሆን ለማበረታታትና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ ካሉት 12 ተፋሰሶች ውስጥ አንዱ የሆነውን የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን መ/ቤት እና የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 253/2003 ዓ.ም ተቋቁሟል፡፡ ተጠሪነቱም ለተፋሰሶች ባለሥልጣን ከፍተኛ ምክር ቤት እና ለውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ነው፡፡

## የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ተግባርና ኃላፊነት

### ራዕይ፡-

12. የተቀናጀ ሁሉን አቀፍ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት የሰፈነበትና የተፋሰሱን ስነ-ምህዳር ሚዛን የጠበቀ ሞዴል ተፋሰስ ሆኖ ማየት፣

### ተልዕኮ፡-

13. በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ፣ አግባብነት ያላቸውን አካላት ያሳተፈ፣ የተፋሰሱን ስነ-ምህዳር ሚዛን የጠበቀ፣ ዘላቂነት ያለውና ሁሉን አቀፍ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት በተፋሰሱ ውስጥ ማስፈንና ተግባራዊ ማድረግ፣

### ዓላማ፡-

14. የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ፍትሃዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማበረታታትና መቆጣጣር ነው፡፡

### ተግባርና ኃላፊነት፡-

15. ባለስልጣኑ በደንብ ቁጥር 253/2003 ዓ.ም መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

- የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፓሊሲ ሀሳቦችን በማመንጨት ለከፍተኛ ምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደትን ለማስፈፀም የሚረዱ ተግባራትን ያከናውናል፤ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በተፋሰሱ ውስጥ ከውሃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶች፣ ተግባራትና መስተጋብሮች በይዘታቸው፣ በጊዜ ሠሌዳቸው፣ በውጤታቸውና በአመራራቸው ከተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
- የተፋሰስ ዕቅድ በማዘጋጀት ለከፍተኛ ምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- ለክልሎች በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተፋሰሱ ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ በአዋጅ ቁጥር197/2000 አንቀጽ፲፭ (15) መሠረት ይሰጣል፤ በፈቃድ አሰጣጥ የተመለከቱ ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
- በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፤ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያጠናክራል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤
- የተፋሰሱን ውሃ ሀብት ስትራቴጂክ ዕቅድና የውሃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራትና ለመደገፍ እንዲያስችል የተፋሰስ ሞዴል ያዘጋጃል፤ ይጠቀማል፤
- የውሃ ምደባና አጠቃቀምን ስለሚመለከቱ አለመግባባቶች አፈታት ለከፍተኛ ምክር ቤቱና ለሚኒስቴሩ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
- አግባብ ባላቸው አካላት መካከል ውጤታማ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
- ከተጠቃሚዎች የውሃ ክፍያ ይሰበስባል፤
- ከሌሎች አገሮች ጋር ድንበር ዘለል ወንዞችን በሚመለከት ለመወያየት አግባብ ላለው አካል በከፍተኛ ምክር ቤቱ መመሪያ መሠረት አስፈላጊ እርምጃዎችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፤
- ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችንና ምርምሮችን ያካሂዳል፤
- በመስኖ ልማት ሥራዎችና ፕሮጀክቶች አካባቢ ጨዋማነት እንዳይከሰት የከርሰ ምድር ውሃ እንቅስቃሴን በመቆጣጠር እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

- የወንዝ አቅጣጫ አመራር ሥራ ይሠራል፤
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
- ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል::

## የባለሥልጣኑ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል፡-

## አደረጃጀት

16. የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን ተጠርነቱ የአዋጁ አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች የሚሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ለተፋሰሱ ከፍተኛ ምክር ቤት እና በሥልጣንና ተግባሩ ሥር በሚወድቁ ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ለውሃ፤መስኖና ኤሌክትሪክ ሚ/ር ሲሆን በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ተቋም ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ የሆኑ ስምንት ዳይሬክቶሬቶች፣ አንድ ማስተባበሪያ (ላይዘን) ጽ/ቤት መቀመጫው አዲስ አበባ ከተማ እና ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አሉት፡፡ ዝርዝር የባለስልጣኑን ድርጅታዊ መዋቅር **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

**የሰው ኃይል**

17. ባለስልጣን መ/ቤቱ በታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም በጠቅላላው 114 ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 49 (43%) ሴቶች ሲሆኑ 65 (57%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ ዶክሬት/3ኛዲግር 1 (0.9%)፣ በኤም.ኤስ.ሲ/ኤም.ኤ ደረጃ ያሉ 21 (18.5%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 40 (35%)፣ ኮሌጅ ዲፕሎማ 12 (10.6%)፣ እንዲሁም የቀለም ትምህርት ያላቸው 40 (35%) ሰራተኞች ናቸው፡፡

**የባለስልጣኑ የፋይናንስ ምንጭ፡-**

18. የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን የፋይናንስ ምንጭ ከመንግሥት ግምጃ ቤት የሚመደብ ሲሆን በ2006፣ በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመታት የማዕከላዊ ግምጃ ቤት አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| በጀት ዓመት | የተመደበ በጀት በብር | ሥራ ላይ የዋለ በጀት በብር | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2006 | 4,208,522.48 | 3,147,601.85 | 75% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2007 | 10,000,000.00 | 9,048,669.45 | 90% |
| 2008 | 36,390,000.00 | 31,247,505.73 | 85.8% |

**የሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን የሥራ ፍሰት መግለጫ** (process description)

19. የሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን ሥራን የሚከናወንበት የአሰራር ፍሰት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርቧል፤

- የተፋሰስ ማስተር ፕላንና የተፋሰስ ዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀት፣
- የክትትልና ግምገማ ሰነድ ማዘጋጀት፣
- ለላቀ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የሚውል ዘላቂነት ያለው የውሃ ሀብት ማቅረብ፣
- የውሃ አጠቃቀም ፍቃድ ምደባና ቁጥጥር ማከናወን፣
- የመስኖ ውሀ አቅርቦትን ማዘጋጀት፣
- ተፋሰሱ በእንክብካቤ መያዙን ማረጋገጥና ደህንነቱን መከታተል፣
- የወንዝ አቅጣጫ አመራር ስራ መስራት፣
- ሐይቆችን ከደለል፣ ከብክለትና ከብክነት መጠበቅ፣
- የውሃ ሙላትና የጎርፍ አደጋን መከላከል፣
- የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስራ መስራት፣
- በጥናትና ምርምር የተደገፈ የተፋሰስ መረጃ ማቅረብ፣

**የኦዲቱ ዓላማ ፡-**

20. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ፍትሃዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን የማበረታታትና የመቆጣጣር እንዲሁም በክልሎች እና በባለድርሻ አካላት የሚከናወኑ የሐይቆች እንክብካቤና ልማት የተፈጥሮ ይዘታቸውን ሳይለውጡ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን ማረጋገጥ ሲሆን፤ ይህንን በተመለከተ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውጤታማ አፈጻጸም እንዲኖረው ሊያደርጉ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ነው፡፡

**የኦዲት አካባቢ**

21. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area) በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን "የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ እና የውሃ ሀብት አስተዳደር አፈጻጸምን የሚመለከት ነው፡፡

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች፡-**

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ**

22. በተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area) ሥር 3 (ሶስት) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ የምደርሰውን ጉዳት መከላከል የሚያስችል ልማትና እንክብካቤ ተግባራት የተከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
2. በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ፍታዊና አሳታፍ በሆነ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡፡
3. በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ መረጃዎችን ለመጠቀምና ለሚፈልገው ተገልጋይ በብቃት እና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል እንዲሁም ቅንጅታዊ የአሰራር ስረዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፡-**

23. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት አራት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 34 (ሰላሳ አራት) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ -**

24. የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2006-2008 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ  የሥምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማነት" ላይ ሆኖ፤ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በተፈሰሱ ውስጥ በምገኙ እና በተመረጡ

ሁለት ንዑስ ተፋሰሶች (በሀዋሳ እና በዝዋይ ሻላ)፣ በናሙና ተመርጠው በታዩ ከወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤቶች ፣ከውሃ ተጠቃሚ አካላቶች፣ ከከተማ ማዘጋጃ ቤቶች፣ በሐይቆች ዳርቻ ከሚገኙ የንግድ ተቋማት፣ ካአሳ አስጋሪ ማህበራት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን ኦዲቱም የተከናወነው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የየመ/ቤቶቹን የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በቼክ ሊስት በመወያየት እና በማጣራት፣ የባለስልጣን መ/ቤቱን ሥርዓት ለማስፈጸም ሥራ ላይ የዋሉ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስ እና የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች፣ ሐይቆች እና ወንዞች የሚገኙባቸውን ቦታዎች በአካል ተገኝቶ በመገምገም ነው፡፡ (ዝርዝር በናሙና ተመርጠው የታዩ ቦታዎች በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡)

## ክፍል ሁለት

### የኦዲቱ ግኝቶች

### ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ ስነ- ምህዳርን ከውድመት መከላከሉን በተመለከተ፡-


25. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ ስነ- ምህዳርን ከውድመት ለመከላከል የሚስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ እና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች ሥር በሚገኙ ወረዳዎች፣
    - በተለያዩ ምክንያቶች መሬት መቦርቦርና አፈር መሸርሸር እየጨመረ መምጣቱ፣
    - በህጋዊም ሆነ በህገ ወጥ መንገድ ከተራራማ ቦታዎችና ከተቦረበሩ መሬቶች አሸዋ እየወጣ ያለ መሆኑን፣

27. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997ን በሚቃረን መልኩ ተዳፋትነታቸው ከ60 ፐርሰንት በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶች ተራራማ ቦታዎች የሚታረሱና ለልቅ ግጦሽ እየዋሉ መሆኑን፣ እንዲሁም በዝዋይ ሻላ ተፋሰስ ውስጥ በሚገኙ 469 ንኡስ ተፋሰሶች ውስጥ 57,505 ሄክታር የተጎዳ መሬት (በጣም ገላጣ አካባቢዎች፣ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ቦሮቦሮች እና ገደላ ገደል የበዛባቸው፣ አፈሩ እየተሸረሸረ ወደ ሀይቆችና ወንዞች የሚገባ) መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ ቃለ-መጠይቅ ከቀረበላቸው ከወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤቶች፣ ከውሃ ተጠቃሚ አካላቶች እና በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. ለማሳያ ያህል እ.ኤ.አ. ከ2000 - 2011 ዓ.ም ድረስ፡-
    - የላንጋኖ እና የአብጃታ ሐይቅ በቅደምተከተላቸው 4.0 ኪ.ሜ$^2$ እና 38.3 ኪ.ሜ$^2$ የቀነሱ መሆኑ፣ በሁለቱም ሐይቆች አከባቢ የጥቅጥቅ ደን ሽፋን በ9.0 ኪ.ሜ$^2$ መቀነሱ፣ በተቃራኒው የእርሻ፣ የሳር እና የግጦሽ መሬት በላንጋኖ 43.0 ኪ.ሜ$^2$ እና በአብጃታ122.5 ኪ.ሜ$^2$ መጨመሩ፣
    - የዝዋይ ሐይቅ በአማካይ ጥልቀት ከ2007 ዓ.ም በፊት 4 ሜትር የነበረው ሲሆን አሁን በአማካይ 2.5 ሜትር ጥልቀት ያለው መሆኑ፣

- የጨለለቃ ሐይቅ ከሐዋሳ ሐይቅ ጋር አንድ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ የግጦሽና አሸዋ የማውጣት ሥራ የሚከናወንበት መሆኑ፣ (የመጥፋት ሂደቱ ማሳያ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡)




**የጨለቅለቃ ሓይቅ መጥፋት**

**ምንጭ:** Tripartite cooperation project among Hawassa University, Rift Valley Lakes Authoritty and Hawassa City Administration, October, 2015

- እንዲሁም በአባያ ጫሞ ንዑስ ተፋሰስ የወይጦ ወንዝ በታችኛው ተፋሰስ እና በሎካ አባያ ወረዳ ቡኪቶ በሚባል ቀበሌ 2500 ሄ/ር መሬት በላይ ለኢንቨስተሮች በመሰጠቱ ደን በከፍተኛ ሁኔታ የተጨፈጨ መሆኑን በኦዲቱ ውቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡





**ፎቶ ቁጥር አንድ ፡- በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስበ ዝዋይ ሻላ ንዕስ ተፋሰስ**

**በአርስ ነገሌ ወረዳ ሻላ ቢላ ቀበሌ ከፍቄ ተራራ በሚነሳ ጎርፍ የተፈጠረ እና ከፍተኛ ስፋትና ጥልቀት ያለው ወደ አብያታ ሀይቅ የሚፈስ ገሊ/ቦርቦር**

**በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ በሄሬራ ቀበሌ ምንም አይነት የተፋሰስ ልማት እና እንክብካቤ ሥራ ያልተከናወነበት እና ከፍተኛ ስፋትና ጥልቀት ያለው ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚፈስ ገሊ/ቦርቦር**



**ፎቶ ቁጥር ሁለት ፡- በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ሀዋሳ ንዕስ ተፋሰስ በቱላ ክፍለ ከተማ ሐቤላ ወንዶ ቀበሌ እና ከፍተኛ ስፋትና ጥልቀት ያለው ወደ ሀዋሳ ሀይቅ የሚፈስ ገሊ/ቦርቦር**

29. ጉዳዩ የሚመለከታቸው በናሙና የታዩ የወረዳ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ስነ ምህዳርን ከውድመት ለመከላከል ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር የተጀመሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች መኖራቸውን፣ ነገር ግን ስለ ስነምህዳር ጥበቃና ጥቅም በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ከፍታ ያላቸው ቦታዎችና በፊት ምንጭ የሚፈልቅባቸው ስፍራዎች የሚታረሱ መሆኑን፣ የደን መጨፍጨፍ እና የአፈር መሸርሸር በስፋት መኖሩን፣ የሚሰሩ የልማትና እንክብካቤ ስራዎችን በበላይነት የሚጠብቅ አካል ባለመኖሩ ችግሩን ለመከላከልም ሆነ ለመቀነስ አለመቻሉን የገለጹ ቢሆንም እነርሱም ሥራውን በበላይነት የማከናወን ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ምክንያቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

30. ስለ ሁኔታው የባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በቃለ በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፤ የተዘረዘሩት ችግሮች መኖራቸውን የሚያውቁ መሆኑን፣ ነገር ግን መ/ቤቱ በቅርብ ጊዜ ስራ ከመጀመሩ ጋር ተያይዞ ዋና ስራቸው የነበረው በተፋሰሱ መረጃ ማሰባሰብ፣ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራትና ጎን ለጎን የተፋሰስ ልማት ስራን መጀመር እንደ መፍትሄ የተወሰደና በተፋሰሱ በሁሉም ወረዳዎች ለመስራት የአቅም ውስንነት ያለ በመሆኑ ጠንካራ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

31. ስነ- ምህዳርን ከውድመት ለመከላከል የሚስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ካልተደረገ በተፋሰሱ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የደን መጨፍጨፍ(deforestation) እና የአፈር መሸርሸር እንዲጨምር የሚያደርግ እና ጨፌና ረግረጋማ ቦታዎች፣ እንዲደርቁ በማድረግ የሐይቆች ስነ-ምህዳር ስርዓት መናጋት በውስጣቸው የሚገኙ ብዝሃ-ህይወት መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

## በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ውስጥ የሚገኙ የተፋሰስ አካባቢዎች ጥበቃ በተመለከተ፡-

32. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ውስጥ የሚገኙ የተፋሰሱ አከባቢዎች ያሉበትን ሁኔታ ሊያጠና እና በጥናቱ መሰረት ጉዳት የደረሰባቸውን አከባቢዎች ሊለይ ይገባል ፡፡ የተለዩት አካባቢዎች ግልጽ የሆነ የመመረጫ መስፈርት በማዘጋጀት እንደጉዳታቸው መጠን በመለየትና ቅደም ተከተል በማውጣት የማልማትና የማንከባከብ ስራ ሊከናወንባቸው ይገባል፡፡

33. በባለሥልጣኑ በሶስት ንዑስ ተፋሰሶች (ሀዋሳ ፣ዝዋይ ሻላ  እና አባያ ጫሞ )  ላይ ንዑስ ተፋሰሶቹ ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቱ መሰረት የተለያዩ ጉዳት አይነትና መጠን ያላቸው እና ከሐይቆች ወይም ከውሃ አካላት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው አካባቢዎች ለማልማትና ለማንከባከብ ቅድሚያ ለመስጠት ግልጽ የሆነ መምረጫ መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው ከታዩ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤቶች በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ከወይጦ ወንዝ ጋር ተያይዞ በክልሉ መስተዳደር አስተባባሪነት ባለስልጣን መ/ቤቱን ጨምሮ ከፌዴራልና ከክልል በተወጣጡ ባለሙያዎች ተደርጎ በነበረው ጥናት ላይ የተቀመጡ የአጭር ጊዜ ማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ የመጀመሪያ እርምጃ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር ፎረም መመስረት ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ በጅንካ መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት የተደረገ ቢሆንም ስምምነቱን ሁሉም አካላት ለመተግበር እንቅስቃሴ ያላደረጉ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት በባለሥልጣኑ የተለያዩ እንክብካቤና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ በቱላ ክፍለ ከተማ እና በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የተለያዩ ጉዳት ዓይነትና መጠን ያለውና ከሀዋሳ ሀይቅ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው ተብሎ በ2008 በጀት ዓመት ከተለዩት ውስጥ፡-

- በቱላ ክ/ከተማ በሀበላ ወንዶ ቀበሌ በጫራ ማይክሮ ተፋሰስ ውስጥ ቀጥታ ወደ ሀይቁ የሚፈስና ከፍተኛ ጥልቀትና ስፋት ያለው በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር እያደረሰ ያለው ቦሪቦሪ /ገሊ/  ምንም አይነት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ሥራ ያልተደረገለት መሆኑን፣
- በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ በጋሎ አርጌሳ ቀበሌ ከሩኬሳ ሱኬ፣ መቅባሳ ቆርኬ፣ ኦዶ ወጣጬ ቀበሌዎች የሚነሳ ጎርፍ ሞሌ በሚባል ቦታ ተገናኝቶ ቀጥታ ወደ ሀይቁ የሚገባ እና ጎርፉ የፈጠረው ገሊ በግምት 20-30 ሜትር ስፋት እና 5-10 ሜትር ጥልቀት ያለው ቢሆንም ምንም አይነት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ያልተደረገለት መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት በተደረገው መስክ ምልከታ እና  ለፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች በተደረገ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ በዝዋይ ዱግዳ፣ በጥዮ፣ በኣዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ፣ በአርሲ ነገሌ ወረዳዎች የተለያዩ ጉዳት ዓይነትና መጠን ያለቸውና ከሀይቆች (ዝዋይ፣ አብጃታና ሻላ ) ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው ተብሎ በ2008 በጀት ዓመት የተለያዩ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራዎች የተከናወኑባቸው ቀበሌዎች ቢኖሩም፤

- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ በበሺራ ጫፋና በሄሬራ ቀበሌዎች መካከል የሚገኝ በሳቀላ ተፋሰስ ከተለያዩ አካባቢዎች በሚመጣ ጎርፍ የተፈጠሩ ትላልቅና ሰፋፊ ቦርቦርዎች ያሉና ደለልን ይዞ ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገቡ ቢሆንም ምንም አይነት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራ ያልተሰራ መሆኑን፣
- በጥዮ ወረዳ ብዙ ምንጮች የሚፈልቁበትና በአካባቢው ህብረተሰብ ጉዳት እየደረሰበት የሚገኘው ጭላሎ ተራራ ላይ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራ ያልተሰራ መሆኑን፣
- በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ አባዬ ደነባ ቀበሌ ከፍተኛ ጥልቀትና ስፋት ያለው ገሊ /ቦሪቦሪ/ ከዝዋይ ሀይቅ ጋር ቀጥተታ ግንኙነት ያለው ቢሆንም ከፍተኛ ወጪ ያስፈልጋል በሚል የ2008 በጀት ዓመት ፕሮጀክት ውስጥ ያልተካተተ መሁኑን፣ እንዲሁም
- በአርሲ ነገሌ ወረዳ በሻላ ቢላ ቀበሌ በፍቄ ንዑስ ተፋሰስ ፍቄ ከሚባል ተራራ በሚነሳ ጎርፍ የተፈጠረው ገሊ/ቦርቦሪ/ ስፋቱ በግምት 15-20 ሜትር የሚሆን እና ጥልቀት ያለው ሲሆን ከፍተኛ ደለልን ወደ አብጃታ ሀይቅ የሚወስድ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት የተቀረጸው ፕሮጀክት ውስጥ አለመካተቱን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው መስክ ምልከታ እና ከፕሮጀክት አስተባባሪዎች ገለጻ ለማወቅ ተችሏል፡፡



ፎቶ ቁጥር ሶስት በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ በሀዋሳ ንዕስ ተፋሰስ በሀዋሳ ዙርያ ጋሎ አርጌሳ ቀበሌ የሚገኝ እና ከፍተኛ ስፋትና ጥልቀት ያለውና በቀጥታ ወደ ሀዋሳ ሀይቅ የሚፈስ ገሊ/ቦሪቦሪ

37. ስለጉዳዩ በናሙና በታዩ ወረዳዎች የወረዳ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎችና ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ውስጥ የሚገኙ የተፋሰሱ አከባቢዎች ያሉበትን ሁኔታ ስለመጥናቱ እና በ2008 በጀት ዓመት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ፕሮጀክት አካል የነበሩ ቀበሌዎች የተመረጡበት ሂደት የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ፕሮጀክት ከመቅረጹ በፊት ወደ ሀይቆች የሚገባውን ደለል ለመቀነስ በሚል ለሐይቆች ቅርበት ያላቸውና ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ቀበሌዎች በሀይቆች ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት በተደረገ የመስክ ምልከታ እንጂ በጥናት ላይ ተመስርቶ እና መመረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ የተመረጡ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

38. ስለ ጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው፣ በተፋሰሱ ውስጥ የተጎዱ ቦታዎች በጉዳት አይነትና መጠናቸው የአፈርና ውሃ እንክብካቤ ሥራ በሚጠይቀው ሳይንሳዊ መስፈርት መሰረት እንዲመረጡ ያልተደረገበትን ምክንያት መጀመሪያ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን ለመስራት ምንም መስፈረት የሌላቸው መሆኑን፣ ሁሉም ቦታ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ሥራዎች እንደ ዘመቻ መጀመራቸውን፣ መስፈርቱን ለማዘጋጀት ተፋሰሱን ሙሉ በሙሉ ማጥናት ስለሚያስፈልግ በተፋሰሱ ውስጥ ባሉ 192 ወረዳዎች ጥናት ለማድረግ የሎጅስቲክና የሰው ሀይል እጥረት መኖሩን ችግሩ በራሱ መስፈርት ሊሆን እንደሚችል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በፕሮጄክት ተይዘው የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ለመስራት የተመረጡ ቦታዎች በመስክ ምልከታ የታዩት እና ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው የመመረጫ መስፈርት በማዘጋጀት በቅደም ተከተል ግልጽ በሆነ መንገድ መመረጥ የነበረባቸው በመሆኑ ምክንያቱን ለመቀበል ያዳግታል፡፡

39. በተፋሰሱ ውስጥ የተጎዱ ቦታዎች በጉዳት አይነትና መጠናቸው በመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች አንጻር እንዲሁም ከጉዳታቸው አኳያ ቅድሚያ ተሰጥቶ ግልጽ በሆነ መመረጫ የልማትና እንክብካቤው ሥራው ካልተከናወነ በህብረተሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዳይኖር እና

ቅድሚያ መሰራት ያለበት ባለመሰራቱ የተሰሩ አካላዊና ስነ ህይወታዊ የተፈጥሮ እንክብካቤ ሥራዎች እንዲወድሙ ያደርጋል፡፡

**ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ሥራዎች ቀጣይነት እንዲኖረው መደረጉን በተመለከተ፡-**

40. በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የሚሰሩ የልማትና የእንክብካቤ ስራዎች ደረጃቸውን የጠበቁና ዘላቂነታቸው በተረጋገጠ መልኩ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ሥራዎቹም የተቀናጀና ቀጣይነት ያላቸው እንዲሆኑ በየጊዜው ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን መከታተል/መገምገም ይኖርበታል፡፡

41. በተፋሰሱ ውስጥ በባለስልጣን መ/ቤቱ ድጋፍ የተሰሩ የስነ አካላዊ (physical structures) እና የስነ ህይወታዊ (biological conservation) ስራዎች በቅንጅት እንዲደጋገፉ አለመደረጉ እንዲሁም ክትትል የማይደረግላቸው መሆኑን በሀዋሳና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ ተመርጦ በታዩ በወንዶ ገነት፣ በጥዮ፣ በዝዋይ ዱግዳ፣ በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻና በአርሲ ነገሌ ወረዳዎች እና በሀዋሳ ከተማ፣ በቱላ ክፍለ ከተማ፣በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

42. ለአብነት፡- በሐዋሳ እና ዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች፡-

- አገልግሎት መስጠት እንደጀመሩ የፈረሱ መሆኑን፣
- የክትር (ጋቢዮዎን) ስራዎች የጎርፍ ግፊት መጠን /discharge rate/ ሳይጠና የተሰሩ አካላዊ ስራዎች ርቀታቸውን /interval/ ጠብቆ አለመሰራታቸውን፣
- በተሰራው ጋቢዎን አልፎ የሚፈስ ውሃ የሚያርፍበት ቦታ /Apron/ ያልተሰራ በመሆኑ ተጨማሪ መሬት መቦርቦር እያስከተለ መሆኑን፣
- እንዲሁም በየጊዜው የችግኝ ተከላ በተፋሰሶቹ ውስጥ የሚከናወን ቢሆንም በአብዛኛው የማይጸድቁ (low survival Rate) መሆኑን ለምሳሌ በወረዳዎች የችግኞች ተከላ ውጤታማ ነው እየተባለ በሪፖርት የሚገለጸው በአካል ሲታይ ችግኞቹ የጸደቁ አለመሆናቸው መታየቱ እና
- በአርሶ አደሩ ተሳትፎ በተፋሰሱ ውስጥ የሚከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በየዓመቱ የሚታረሱና የሚበላሹበት ሁኔታ መኖሩን፣ በኦዲቱ ወቅት በመስክ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ከወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡



**ፎቶ ቁጥር አራት፡- በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን በሀዋሳ ንዕስ ተፋሰስ በወንዶ ገነት ወረዳ በኦዶ ቀበሌ በፕሮጀክቱ የተሰራ ጋቢዮን አገልግሎት መስጠት ሳይጀምር የፈረሰ፤**



**ፎቶ ቁጥር አምስት፡- በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን በሀዋሳ ንዕስ ተፋሰስ ሀዋሳ ዙርያ ወረዳ በጋሎ አርጌሳ ቀበሌ በፕሮጀክቱ የተሰራ ጋቢዮን አገልግሎት መስጠት ሳይጀምር የፈረሰ፤**

43. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለ ሁኔታው በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በሚሰሩ ስራዎች ቀጣይነት ላይ ብዙ ችግሮች እንዳሉ የሚያውቁ መሆኑን፣ ቅንጅት ለመፍጠር ብዙ መድረኮችን አዘጋጅተው ግንዛቤ እየሰጡ ያሉበት ሁኔታ ቢኖርም ወደ ስራ የመተግበር ችግር መኖሩን እና በወረዳ ደረጃ መዋቅር የሌላቸው በመሆኑ ሥራዎችን በቅርበት መከታተል አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በተፋሰሱ ውስጥ የሚሰሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ቀጣይነት በየደረጃ ካሉ አስተዳደሮች ጋር ለመቀናጀት የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ሊረጋገጥ ስለሚገባ ምክንያቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

44. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ሥራዎችን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ቀጣይነት እንዲኖራቸው አለማድረጉ የተፈጥሮ ሀብቱ ለከፋ ጉዳት እንዲዳረግ ከማድረጉም ባሻገር መንግስት ለዘርፉ የሚመድበው ገንዘብና የህብረተሰቡ ጉልበት እንዲባክን ያደርጋል፡፡

**ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀይቆች ላይ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮች የሚደርሱትን ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል የሚረዳ መመሪያ/ ማንዋል ማዘጋጀቱን በተመለከተ፡-**

45. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ የውሃ ሀብት ልማትና ብዝሀ ህይወትን ለማስተዳደር የሚረዳ የአፈርና ውሃ ጥበቃ መመሪያ /Guideline/ በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨትና ተግባራዊ መደረጉን መከታተል ይኖርበታል፡፡

46. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ በሀይቆችና ወንዞች ላይ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮዊ ችግሮች የሚደርሱትን ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል የውሃ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚረዳ መመሪያ ወይም የትግበራ ማንዋል አለመዘጋጀቱን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

47. በናሙና ተመርጠው በታዩ ዝዋይ ሻላ እና ሐዋሳ ንኡስ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ እና ባለሥልጣኑ ፕሮጀክት ቀርጾ እያከናወናቸው ባለባቸው ወረዳዎች (ቱላ ክፍለ ከተማ፣ ወንዶ ገነት፣ ሀዋሳ ዙሪያ፣ ጥዮ፣ ዝዋይ ዱግዳ፣ አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ እና አርሲ ነገሌ) የሚገኙ ባለሙያዎች የፕሮጀክቱ አካል በሆነው በእያንዳንዱ ስራዎች ላይ የባለስልጣን መ/ቤቱ እና የወረዳዎች ተግባርና ኃላፊነት የማይታወቅ ወይም በግልጽ ያልተቀመጠ መሆኑን፣ እንዲሁም በወንዶ ገነት፣ በሀዋሳ ዙሪያ፣ በዝዋይ ዱግዳ፣ በአርሲ ነገሌ ወረዳዎች የወረዳ ባለሙያዎች በፋይናንስ ኮድና መመሪያ አጠቃቀም ላይ የክህሎትና የዕዉቀት ክፍተት መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. ስለጉዳዩ የባለሥልጣኑ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራዎችን ለመምራት የሚረዳ መመሪያ /ጋይድላይን/ በባለሥልጣን መ/ቤቱ ደረጃ አለመዘጋጀቱን፣ ሆኖም የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመራው በwatershed

management guideline መሰረት ስለ ሆነ ወደ ፊት ይህን ጋይድላይን እንደሚያሰራጩ ገልጸዋል፡፡

49. በሀይቆችና ወንዞች ላይ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮዊ ችግሮች የሚደርሱትን ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል ለሚያከናወነው የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ስራዎችን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚረዳ መመሪያ ወይም የትግበራ ማንዋል አለመዘጋጀቱ የሚሰሩ ስራዎች ወጥ እና የሚፈለገውን ደረጃና ጥራት ጠብቀው እንዳይከናወኑ በማድረግ ውጤታማ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ግልጽ የሆነ የኃላፊነት እና የተጠያቂነት ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

**በተፋሰሱ የውሃ አካላትን፣ ሐይቆቹንና የብዝሀ ሕይወቱን ሕልውና ከብክለት መከላከልን አስመልክቶ፡-**

50. ከከተሞችና እንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ የተፋሰሱን አካባቢውን በማይጎዳ መልኩ ማዘጋጀትና ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዞችና ሐይቆች ከመልቀቃቸው በፊት ቆሻሻዎቹ መታከማቸው የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ሀይቆቹንና የብዝሀ ህይወቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ አሉታዊ ተጽኖዎችን የመለየት፣ የመቀነስና የመከላከል ስራን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

51. ከከተሞችና እንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች ወደ ወንዞች ከመለቀቃቸው በፊት ከባለሥልጠኑ አክሞ ለመልቀቅ ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው ቢሆንም፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ ውስጥ

- በናሙና የታዩ ድርጅቶች ከቢ.ጂ.አይ (BGI) ኢትዮጵያ ፒ.ኤል.ሲ (ሀዋሳ ቢራ ፋብሪካ)፣ ኢታብ ሳሙና ፋብሪካ፣ ታቦር ሴራሚክ ፋብሪካ፣ ሞሃ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣ እና ከሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከምርት ክፍሎች የሚወጣው ብክለት ያለው ፍሳሽ በጨፌ ረግረጋማ መሬት አማካኝነት በጥቁር ውሃ ወንዝ በኩል ወደ ሀዋሳ ሀይቅ የሚገባ መሆኑን፣ በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ እና ዝዋይ ሐይቅ ላይ ህጋዊም ሆነ ህገ ወጥ የአሳ አስጋሪዎች የሚበዙና የአሳዎች ተረፈ ምርት መልሶ ወደ ሐይቆቹ የሚጣል መሆኑን፣



ፎቶ ቁጥር ሰባት፡- በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ ከፋብሪካ ከምርት ክፍሎች የሚወጣው ብክለት ያለው ፍሳሽ ቆሻሻ እና በጋሎ አርጌሳ ቀበሌ ዴላ ገበያ አካባቢ የአሳዎች ተረፈ ምርት መልሶ ወደ ሐይቆቹ የሚጣልበት ቦታ

- ዝዋይ ሻለ ንዑስ ተፋሰስ ውስጥ በናሙና የታዩ በዝዋይ ከተማ ከመስኖ እርሻ ማሳ እና ከአበባ ልማት ድርጅቶች ሼር ኢትዮጵያና በሼር ኢትዮጵያ ቅጥር ግብ ውስጥ ከሚገኙ Herburg Roses Plc, AQ Roses, Zway Roses የሚወጣ ፍሳሽ ኬሚካል ቆሻሻ ሳይታከም ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባ መሆኑን፣
- በአዳሚ ቱሉ ጅዶ ኮምቦልቻ ወረዳ በዝዋይ ሐይቅ ዙሪያ ከፍተኛ የመስኖ ተጠቃሚዎች ያሉ ሲሆን የተለያዩ ያልተፈቀዱ ኬሚካሎችን ስለሚጠቀሙ በዝናብ ወቅት በጎርፍ እና በመስኖ ቦይ አማካኝነት ኬሚካሉ ወደ ሐይቁ የሚገባ መሆኑን እንዲሁም
- በምስራቅ ዝዋይ ማይክሮ ተፋሰስ ውስጥ ከአሰላ ከተማ የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻዎች የሚደፉበት ቦታ ምቹ ባለመሆኑ ቆሻሻዎች በዝናብ ወቅት በተለይ በክረምት ወልኬሳ ወደ ሚባል ወንዝ ገብቶ የካታርን ወንዝ በመቀላቀል ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባና የሚበክል መሆኑን እና
- ከዝዋይ እና ከመቂ ከተሞች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች የሚደፉበት ቦታ ምቹ ባለመሆኑ ቆሻሻዎች ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባና የሚበክል መሆኑን፣
- ለባቱ (ዝዋይ) ከተማ ለመጠጥ ውሃ ሲያገለግል የነበረው የዝዋይ ሀይቅ በነዚህ ችግሮች ምክንያት በመበከሉ የከተማው ነዋሪዎች የከተማውን ውሃ መጠቀም ማቆማቸውን መግለጻቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡



**ፎቶ ቁጥር ስምንት፡- በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ ከአበባ ልማት ድርጅቶች (ሼር ኢትዮጵያ፣ Herburg Roses፣ AQ Roses እና Zway Roses) የሚወጣ ፍሳሽ ኬሚካል ቆሻሻ በቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ ሲገባ የሚያሳይ፤**

52. *ስለጉዳዩ የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎችና የወረዳ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ በሀዋሳ እና ዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ ተመርጦ በታዩ ወረዳዎች ሀይቆቹና የብዝሀ ህይወቱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደሩ ያሉ ችግሮች መኖራቸውን የሀይቁ ዳርቻ የሚታረስ በመሆኑ ወደ ሀይቁ በሚገባ ደለል ምክንያት የአሳ ምርት መቀነሱና ከእርሻ ማሳዎች ወደ ሀይቁ በሚገቡ ኬሚካሎች ምክንያት ብዝሀ ህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆኑንና ችግሩን ለመከላከል እስካሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡*

53. *ስለ ሁኔታው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በተፋሰሱ የሀይቆቹንና የብዝሀ ሕይወቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ ብዙ አሉታዊ ተጽዕኖዎች መኖራቸውን፣ ተጽዕኖዎችን ለመከላከል ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አለመቻሉን እንዲሁም ቆሻሻን አክሞ ስለአለመልቀቃቸው ድርጅቶቹ ቀድመው የተቋቋሙ በመሆኑ በወቅቱ ይህን የሚያክም መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን ገልጸው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ይህን የሚሰራ ክፍል የተቋቋመ በመሆኑ ለወደፊት ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡*

54. *ሀይቆቹንና የብዝሀ ህይወቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ አደገኛ ፍሳሾችና ኬሚካሎች ሳይታከሙ ወደ ወንዞች እና ሐይቆች መለቀቃቸው እንዲሁም አሉታዊ ተጽኖዎችን ለመቀነስና ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት*

አለመሰራቱ፣ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ሀይቆች ብክለት መጠንና ብክለት መንስኤዎች እንዲጨምርና ሀይቆች ውስጥ ያሉ ብዝሀ ህይወቶች ለአደጋ እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

## በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የአከባቢ ተጽኖ ግምገማን እና የግንዘቤ ሥራን በተመለከተ፡-

55. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የሚያከናውኑዋቸውን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ አስተያየት ሊሰጥ ይገባል፡፡ በሚከናወኑት የልማት ሥራዎች እና ኢንቨስትመንት ላይ ክትትል በማደረግ ሊያደርሱ የሚችሉ ተጽዕኖች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች በሚያሰጡኑዋቸው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ የውሃ አካላቱን ደህንነት በዘላቂነት የተጠበቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ሆነው መጠናታቸውን እንዲያረጋግጥ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት አስተያየት እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በሐይቆችና በረግረጋማ መሬቶች አካባቢ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት ላይ ክትትል በማደረግ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እና ግንዛቤ ያልሰጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ እንደ ተቋም የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ለመገምገም ስልጣን የሌላቸው እና አስተያየት እንዲሰጡ የማይደረጉ እና ስለኢንቨስትመንት የሚያውቁት የውሃ መጠቀም ፈቃድ ለመውሰድ ከመጡ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

59. በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የሚያከናውኑዋቸውን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ አስተያየት ባለመስጠቱና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አለመስራቱ፣ ፈቃዱ የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ስራዎች በውሃ አካላቶቹ ላይ ጉዳት ለመቀነስ ምን እንደታሰበ ሊያውቅ እንዳይችልና እና በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ላይ

የተመለከቱት ነጥቦች መተግበራቸውን ለመቆጣጠርና ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ እንዳይሰጥ ያደርገዋል፡፡

**በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች ሥራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ስለመደረጉ፡-**

60. ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ተግባር ሊሸጋገሩ ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በታዩት

- በሁሉም ወረዳዎች በባለስልጣኑ በጀት ድጋፍ ለሚከናወኑ ስራዎች በጀቱ በጊዜ የማይለቀቅ መሆኑን፣
- በሀዋሳ ከተማ በቱላ ክፍለ ከተማ የክትር /ጋቢዎን/ ስራዎች በ2008 በጀት ዓመት ለማከናወን ድንጋይና ሽቦ ተገዝቶ ሳይሰራበት ለቀጣይ በጀት ዓመት የተላለፈ መሆኑን፣
- በሶስቱም ንዑስ ተፋሰሶች ውስጥ የችግኝ ተከላን በተጎዱ ቦታዎች፣ በተሰሩ እርከኖች እና በሌሎች ቦታዎች ላይ ለመትከል 19.5 ሚሊዮን ችግኞች ታቅዶ 4.48 ሚሊዮን ችግኞች (23%) ብቻ የተከናወነ መሆኑን፣
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ በሂሬራ ቀበሌ እና በወንዶ ገነት ወረዳ በ3 (አባዬ፣ ወተራ ቀጨማ፣ ዩዎ) ቀበሌዎች በ2008 በጀት ዓመት ለመስራት የታቀዱ ስራዎች ያላለቁ መሆኑን፣
- በፕሮጀክት አፈጻጸም በአባያ ጫሞ ንዑስ ተፋሰስ ጨንቻ እና አባያ በመካከለኛ፣ አ/ምንጭ ከተማ፣ በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ- ቱላ ክፍለ ከተማ እና ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ፣ በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ- አርሲ ነጌሌ፣ ሁልባረግ እና ቆሬ ወረዳዎች ዝቅተኛ አፈፃፀም ያስመዘገቡ መሆኑን፣
- በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ሀይቁ ዙሪያ ያለው ህብረተሰብ ከሀይቁ ጥገኝነት ለማላቀቅ ሲባል ስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች የፕሮጀክቱ አካል በማድረግ ቀጣይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ እንዲኖር የሚያደርግ ሲሆን በወረዳው የተሰራጨው የንብ ቀፎና የከብቶች መኖ ግን ሀይቁ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው እና ለስራ አጦች ሳይሆን የተሻለ ኑሮ ላላቸው ሰዎች የተሰጠ መሆኑን፣ እንዲሁም በቱላ ክፍለ ከተማ በ2008 በጀት ዓመት ለስራ

ዕድል ፈጠራ ተብሎ የተገዛ የንብ ቀፎ እስከ መስከረም 2009 ዓ.ም ድረስ ለሚመለከታቸው ያልተሰራጨ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በመስክ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ከወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. ስለጉዳዩ የወረዳ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በባለስልጣኑ በጀት ድጋፍ ለሚከናወኑ ስራዎች በጀቱ በጊዜ ባለመለቀቁና በጀት አመዳደቡ ላይ ብዙ ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች በመኖራቸው ጊዜ የወሰዱበቸው መሆኑን፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ መሰራት ያለበት በበጋ ወቅት ቢሆንም የጋቢዎን ስራዎች ድንጋይና ሽቦ ተገዝቶ ሳይሰራበት ለቀጣይ በጀት ዓመት የተላለፈ መሆኑን እና የችግኝ ዝግጅት እና ችግኝ ከጣቢያው ጭነው ወደ የሚተከልበት ቦታ ለመውሰድ ቦታው በክረምት አስቸጋሪ በመሆኑ ችግር መፈጠሩን ገልጸዋል፡፡

63. የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ባለፈው ዓመት የተሰሩ ስራዎች ፕሮጀክቶቹ ዘግይቶ በመቀረጹ በጀቱም ቶሎ ሊለቀቅ አለመቻሉን፣ ወረዳዎቹ ለፕሮጀክቱ ሥራዎች አዲስ በመሆናቸው ስለ ፕሮጀክቱ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑን፣ ለሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ ብር ቶሎ የተለቀቀ ቢሆንም ቀድሞ የነበረው አሰራር ትክክል ስላልነበር ለማስተካከል ጊዜ መፍጀቱን፣ ከስራ እድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ ችግሮቹ ያሉና የተረዱዋቸው መሆኑን እና ችግሮቹን ለፈጠሩ ወረዳዎች በደብዳቤ ማስጠንቀቂያ የተጻፈላቸው ወረዳዎች ቢኖሩም ለወደፊት ጥብቅ የሆነ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

64. ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ተግባር ባለመሸጋገራቸው የአፈር እና ውሃ ጥበቃ ስራዎች በተገቢው ሁኔታ ተሰርቶ ውጤት እንዳያስመዘግቡ ብሎም ለተጨማሪ የአፈር መሸርሸር እና የሐይቆች በደለል መሞላት ይዳርጋል፡፡

**የረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና የሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀምን በተመለከተ፡፡**

65. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ረግረጋማ መሬቶችና የሐይቆች ዳርቻ በመከለል፣ ወሰኑን የሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት፣ ለረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና ለሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲሁም ደንብና መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

66. ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 ዓ.ም ተቆጣጣሪው አካል አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር በመመካከር እና በመተባበር የተወሰኑ የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ወሰን መከለል እና በተከለሉ የውሃ አካላት ዳርቻዎች ክልል ውስጥ ያሉ እጽዋት ሽፋኖች ወይም ዛፎች እንዳይመነጠሩ ወይም እንዳይቆረጡ እንዲሁም የመኖሪያ ቤቶች እንዳይገነቡ መከልከል እንደሚቻል ቢገልጽም፣ በተፋሰሱ የረግረጋማ መሬት አስተዳደርና የሀይቆች ዳርቻ ክልልን የሚመለከት ጥናት ያልተካሄደ እና የሀይቆች ዳርቻ ክልል (Buffer Zone) እና የረግረጋማ መሬት ወሰን የሚያሳይ ካርታ ያልተዘጋጀ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡



**ፎቶ ቁጥር ዘጠኝ፡- በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ በዝዋይ ሀይቅ ዙሪያ ከብቶች የሚሰማሩበት ቦታ፡፡**

67. በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ እና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች በሚያካልሉዋቸው ወረዳዎች

- በሁሉም የሀይቁ ዳርቻ ክልል ያልተከለለ በመሆኑ ከሀይቁ 5 ሜትር በማይሞላ ርቀት ላይ የሚታረስ እና ከብቶች የሚሰማሩበት መሆኑ፣
- በአርሲ ዞን በጥዩ ወረዳ ጨፌ ሚሶማ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ረግረጋማ መሬት ለባለሀብት ተሰጥቶ እየታረሰ መሆኑን፣
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ 4130 ሄክታር የሚሆን አምስት ረግረጋማ መሬቶች (ሼተ-ማታ-ወደ 300 ሄ/ር፣ ጥኖ- 3000ሄ/ር፣ ወንበራ- 400ሄ/ር፣ ገኖ 30 ሄ/ር እና ዋራቤ- 400ሄ/ር) የሚሆኑና ሁሉም ረግረጋማ መሬቶች ተከልለው ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ ያልሆኑ መሆኑ፣
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳው ሼሌም፣ ውሺቲ እና ዱግዳ አባቱ ቀበሌዎችን የሚያዋስነው ሼተ-ማታ ረግረጋማ መሬት ጥኖ ከሚባል ረግረጋማ መሬት ጋር ተያይዞ ያለ ሲሆን በአሁኑ ወቅት እየታረሰ መሆኑ እና ሼተ-ማታና በአራጣ ቀበሌ ጥኖ ረግረጋማ መሬት አካል የሆነ መሬት ለባለሀብት በመሰጠቱ ለመታረስ ዝግጅት ላይ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት በመስክ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ከወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለ ሁኔታው መጠይቅ የቀረበላቸው የፕሮጀክት አስተባባሪዎችና የወረዳ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ረግረጋማ መሬት ያሉ ቢሆንም በፊት ምንጮች የሚፈልቁባቸው ቦታዎች የደረቁ መሆኑን፣ በፊት ከብቶች የሚሰማሩባቸው የነበሩ ረግረጋማ መሬቶች አሁን እየታረሱ መሆኑን እና ረግረጋማ መሬቶቹን ለመጠበቅና ለማንከባከብ የሚያስችል ምንም አይነት መመሪያ ወይም ደንብ የሌለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

69. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የባለሥልጣን ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ባለፉት ዓመታት ተፋሰሱ ያለበት ሁኔታን በማጥናት ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ነገር ግን በተፋሰሱ የረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና ለሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም ህግ በደንብ መልክ ለማዘጋጀት ዝግጅት ላይ መሆናቸውን እና በየንዑስ ተፋሰሱ ጥናት እያደረጉ በመሆኑ በዚህ ዓመት የሚጠናቀቅ መሆኑን–ገልጸዋል፡፡

70. በተፋሰሱ ለረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና ለሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲሁም ደንብና መመሪያ አለመዘጋጀቱ፤ በተከለሉ የውሃ አካላት ዳርቻዎች ክልል ውስጥ ያሉ እጽዋት/ዛፎች እንዳይመነጠሩ እና

ረግረጋማ መሬት ለእርሻ እንዲውሉ በማድረግ ሐይቆቹ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

**ባለሥልጣን መ/ቤቱ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-**

71. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን ፍትሃዊ እንዲሆን ከሚመለከታቸው የክልልና የወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡ የውሃ አጠቃቀም ጋር ተያይዘው የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

72. በተፋሰሱ በሶስቱ ንዑስ ተፋሰሶች (በሀዋሳ፣ በዝዋይ ሻላ እና በአባያ ጫሞ) ውስጥ የውሃ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ በላይኛውና በታችኛው ተፋሰስ ላይ በሚገኙ ተጠቃሚዎች መካከል የአጠቃቀም ግጭት መኖሩን፣ ለአብነት፡-

- በሻሸመኔ ወረዳ በመስኖ ልማት ስራ እና በመጠጥ ውሃ አጠቃቀም ላይ ግጭቶች ያሉ መሆኑን፣
- በጊዳቦ ተፋሰስ በዳራ ወረዳ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ፍትሃዊ ባለመሆኑ ግጭቶች መኖራቸውን፣ በሎካ አባያ ወረዳ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች በተለይም በብላቴ ወንዝ ላይ በእርሻ ስራ ላይ በተሰማሩ ኢንቨስተሮችና አርሶ አደሮች መካከል ፍትሀዊ የውሃ አጠቃቀም ላይ ግጭቶች ያሉ መሆኑን፣
- በምዕራብ ዝዋይ ንዑስ ተፋሰስ በወንዞች ላይ የሚካሄዱ የመስኖ ተግባራት ፍትሀዊ ባለመሆናቸው በላይኛዉ ተፋሰስና በታችኛዉ የተፋሰሱ ተጠቃሚዎች መካከል አለመግባባት የሚስተዋል መሆኑን፣
- በቡልቡላ ወንዝ፣ ወርጋ ወንዝ፣ መቂ ወንዝና ለመቂ ወንዝ ገባር የሆኑ ሌሎች ወንዞች ላይ በመስኖ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ አለመግባባት የሚስተዋልባቸው መሆኑን እና በአርሲ ነገሌ ወረዳ በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ከፍተኛ የሆነ ግጭት (conflict) ያለ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከተደረጉ መጠይቆች ለማወቅ ተችሏል፡፡

73. ስለ ሁኔታው መጠይቅ የቀረበላቸው የወረዳ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ኃላፊዎች በሰጡት መልስ፤ በየወረዳው አመቱን ሙሉ የሚፈሱና የተለያዩ ጅረቶች ያላቸው ወንዞች ያሉ መሆኑን፣ እንዲሁም የውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን

የሚያደራጀው የመስኖ ልማት ጽ/ቤት ሲሆን የአባላት አመራረጥም ግልጽ ባልሆነ (informal) በሆነ መልኩ መሆኑን እና ቋሚ የሆነ የውሃ ምደባና አጠቃቀም ስርዓት አለመዘርጋቱን ገልጸዋል፡፡

74. ስለ ሁኔታው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ቅሬታዎችን ለመፍታት በአባያ ጫሞ ንዑስ ተፋሰስ ፎረም ለመመስረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመጀመሪያ መድረክ ተዘጋጅቶ ምክክር ያደረገ መሆኑን፣ በመድረኩ የተሰጡትን አስተያይቶች በመውሰድና በማሻሻል በሌሎች ንዑስ ተፋሰሶችም ተግባራዊ እንደሚያደርጉት፣ ወደ ፊት የውሃ ሀብት አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ ፣ ፍትሃዊ ውሃ አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት የውሃ ምደባን ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱን ገልጸዋል፡፡

75. የውሃ ምደባንና ፍትሃዊ አጠቃቀምን የሚመለከቱ አለመግባባቶች የሚፈታበትን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ፍትሐዊ አሳታፊና ዘላቂ በሆነ መንገድ ከተፋሰስ የውሃ ሀብት ሁሉም እኩል ተጠቃሚ እዳይሆን አድርጎታል፡፡

## በተፋሰሱ ውስጥ የሚካሄደውን ውሃ አጠቃቀምን መጠን እና ክፍያ እንዲሁም የፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ሥርዓት መዘረጋቱን በተመለከተ፡-

76. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ውሃ ነክ ስራዎች ለመስራት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥና እድሳት፣ የሚጠቀሙት የውሃ መጠን እና የክፍያ ተመን አወሳሰን ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

77. የውሃ ሀብት አዋጅ 197/1992 አንቀጽ 28/1 ሀ፣ ለ እና ሐ ላይ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በማንኛውም የመንግስት አካል በተሰጠ ፈቃድ ወይም ያለ ፈቃድ የውሃ ሥራዎችን ግንባታ ያካሄደ ወይም የሚያካሂድ፣ በውሃ ሀብት ራሱ በመጠቀም ወይም ለሌሎች ሰዎችን ውሃን በማቅረብ ላይ ያለ እና ቆሻሻን በውሃ ሀብት ውስጥ በመልቀቅ ወይም በመድፋት ላይ ያለ ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጣው ደንብ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ በውሃ ስራዎቹ ወይም በውሃው መጠቀም ለመቀጠል ወይም ቆሻሻን ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ፈቃድ እንዲሰጠው ለተቆጣጣሪው አካል ማመልከት አለበት በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ቁጥር 115/1997 ዓ.ም በመጋቢት 1997 ዓ.ም ወጥቷል፡፡

78. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ለተለያዩ ሥራዎች ውሃን ለሚጠቀሙ የአጠቃቀም ፈቃድ ሊሰጥና በየዓመቱ ፈቃዱን ሊያድስ ሲገባ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች በተፋሰሱ ውስጥ ውሃን የሚጠቀሙ ስለመሆኑ ባለሥልጣኑ ከሰበሰበው መረጃ 319 የውሃ ተጠቃሚዎች ውስጥ

- የውሃ አጠቃቀም ፈቃድ የሰጠው ለ14 መሆኑን፣ ፈቃድ ለማውጣት በሂደት ላይ ያሉት ይህ መረጃው እስከ ተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ 5 ብቻ መሆናቸውን እና ሌሎቹ 300 የውሃ ተጠቃሚዎች (94%) የውሃ ፈቃድ ሳይወስዱ ውሃን የሚጠቀሙ መሆኑን፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ አጠቃላይ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ተጠቃሚዎች (የመስኖ፣ ፋብሪካዎች፣ ሪዞርቶች…) ብዛት እና የሚጠቀሙትን የውሃ መጠን ለይቶ የማያውቅ መሆኑን፣
- በተፋሰሱ ላይ ለተለያየ ሥራ የተተከሉ የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ብዛታቸው እና አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ ባለስልጣኑ መረጃ የሌለው መሆኑን እና
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚያውቃቸው 319 ውሃ ተጠቃሚዎች ውስጥ 86 ተጠቃሚዎችን ብቻ የሚጠቀሙትን የውሃ መጠን (የሜትር ኪዩቢክ ውሃ) የሚያውቅ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

79. በተጨማሪም በውሃ ክፍያ ላይ

- የአከፋፈል ታሪፍ መመሪያ አለመኖሩን፣
- በተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ የውሃ ሀብት የሚጠቀሙ ድርጅቶች የቢ.ጂ.አይ (BGI) ኢትዮጵያ ሀዋሳ ቢራ ፋብርካ፣ የኢታብ ሳሙና ፋብሪካ፣ የሞሃ ለስላሳ ፋብሪካ፣ የሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ የኤልፎራ አግሮ ኢ/ኃ/የተ/የግል/ማ፣ የካስትል ዋይነሪ ኃላ/የተ/የግል/ማ፣ ሼር ኢትዮጵያ ኃላ/የተ/የግል/ማ፣ ሰላም የተፈጥሮ የታሸገ የማዕድን ውሃ ፋብሪካ ወዘተ…) ለሚጠቀሙት ውሃ የሚከፍሉት ክፍያ የሌለ መሆኑን እና
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የውሃ ተጠቃሚዎቹ ለሚጠቀሙት ውሃ የክፍያ ታሪፍ ረቂቅ ጥናት በማጥናት ለሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያላቀረበ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

80. ስለጉዳዩ በኦዲቱ በናሙና የታዩ የውሃ ተጠቃሚ አካላት፣ የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎችና የወረዳ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የውሃ ሀብት አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ በየወረዳው ተግባራዊ አለመደረጉን፣ ውሃን ሁሉም አካል ባስፈለገው ልክ እንደፈለገ የሚጠቀም እና ፍትሃዊና አሳታፊ የሆነ የውሀ ሀብትን የሚከታተል አካል በወረዳ ደረጃ አለመቋቋሙን፣ እንዲሁም በውሃ ለመጠቀም ፍቃድ ለመስጠትም ሆነ ለመከታተል ስለውሃ ሀብት የወጣው አዋጅ ተግባራዊ አለመደረጉን፤ የውሃ ተጠቃሚ አካላትም ለሚጠቀሙት ውሃ ክፍያ የማይከፍሉና ስርዓቱ ስለመኖሩም የማያውቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

81. ስለ ሁኔታው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በተፋሰሱ ያለውን ውሃ አቅም ለማጥናት በስትራቴጅክ ዕቅድ ተይዞ ዘንድሮ በዝዋይ-ሻላ ጥናት ለማካሄድ መታቀዱን ፣ ተቋማቱ የሚጠቀሙት ውሃ መጠን የማይታወቅ በመሆኑ ወደ ፊት ድርጅቶች የሚጠቀሙት ውሃ መጠን ለማወቅ ቆጣሪ በመትከል ለመከታተል ያሰቡ መሆኑን፣ ውሃን በመጠቀም የተለያዩ ልማት ስራዎች ላይ የተሰማሩ ልማት ድርጅቶች የውሃ መጠቀሚያ ፍቃድ ለመውሰድ የሚያስችላቸውን መስፈርቶች (የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት፣ የመሬት ካርታ ወ.ዘ.ተ) ማሟላት አለመቻላቸውን፣ መሬት ተከራይቶ የሚሰሩ ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት ያላስጠኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ባለ ጊዜ መስፈርቶቹን ሳያሟሉ የውሃ ፍቃድ የወሰዱ ልማት ድርጅቶች መኖራቸውን ጠቅሰው የውሃ ክፍያ ረቂቅ መመሪያ በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ አስተያይት እንድንዲሰጡበት ተጠይቀው አስተያየቱን የሰጡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

82. ውሃ ነክ ስራዎች ለመስራት የሚያስችል የፈቃድ ዓሰጣጥና እድሳት እንዲሁም የውሃ መጠን እና ክፍያ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ባለማድረጉ ሀገሪቱ ከዚህ ዘርፍ የምታገኘውን ገቢ ከማሳጣቱ ባሻገር በተፋሰሱ ውስጥ ለልማት የዋለው የውሃ መጠን እንዳይታወቅ እና ፍትሃዊ አጠቃቀም እንዳይኖር አድርጓታል፡፡

**ባለሥልጣን መ/ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ ተፈጥሯዊ ሂደቱን ተከትሎ እየፈሰሰ ስለመሆኑ ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፡-**

83. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ የሚገኙ ወንዞችን ተፈጥሯዊ የፍሰት ሁኔታ አለመዛባቱን የሚከታተልበት ሥርዓት በመዘርጋት መከታተልና መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡

84. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ እና በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰሶች ሥር በሚገኙ ወረዳዎች እና ከተከለሱ ማስረጃዎች

- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ በመከታተል አቅጣጫ የቀየሩ ወንዞችን ወደ መደበኛ ፍሰታቸው እንዲመለሱ እየተከታተለ አስፈላጊውን መፍትሂ የማይሰጥ መሆኑን፣
- በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ ካታር ወንዝን በመቀላቀል ዝዋይ ሀይቅ ሲገባ የነበረው ጩፋ ወንዝ በአራጣ ቀበሌ ጌኖ በሚባል ቦታ አቅጣጫውን በመልቀቅ ወደ 40 ሄክታር የሚሆን የአርሶ አደሩ መሬት ላይ በመተኛት በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን፣
- በኮንሶ አካባቢ የሚገኘው የወይጦ ወንዝ እና በአባያ ጫሞ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኘው የብላቴ ወንዝ አቅጣጫ የቀየረ መሆኑን፣ እና
- የወንዞች ፍሰት የሚቆጣጠር መሳሪያ በተፋሰሶቹ ውስጥ የሌለ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በመስክ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ከወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. ስለ ጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በተፋሰሱ በተለያዩ ምክንያቶች የፍሰት አቅጣጫቸውን የሚስቱና የሚታወቁም የማይታወቁም ወንዞች ያሉ መሆናቸውን እና ወደ ፊት ሙሉ በሙሉ በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ወደ ተግባር የሚገባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡



**ፎቶ ቁጥር አስሪ ፦ በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ ካታር ወንዝን በመቀላቀል ዝዋይ ሀይቅ ሲገባ የነበረው ጩፋ ወንዝ በአራጣ ቀበሌ ጌኖ በሚባል ቦታ አቅጣጫውን በመልቀቅ የአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ተኝቶ ያለበት ሁኔታ፡፡**

86. የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር አለማድረግ የሃይቆች የውሃ መጠን እንዲቀንስ ከማድረጉም ባሻገር ውሃውን በሕገ ወጥ መንገድ ለመጠቀም ለሚፈልጉ የሚያመቻች እና የወንዙ አቅጣጫ በቀየረ ቁጥር በአካባቢው በሚገኙ በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ ውሃው በመተኛት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ያደርሳል፡፡

## ባለሥልጣኑ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨት ለተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት ያቀረበ ስለመሆኑ፡-

87. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨት ለተፋሰስ ምክር ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡

88. ይሁን እንጅ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ እና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያግዙ ሃሳቦችን ለማመንጨት የሚረዱ ጥናቶችን በማከናወን እና ትንተና በመስራት የፖሊሲ መነሻ ሃሰቦችን ለከፍተኛ ተፋሰስ ምክር ቤት ያልቀረበ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

89. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በተፋሰሱ የውሃ ሀብት አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ፈታኝ ሁኔታዎች ያሉ ቢሆንም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያግዙ ሃሳቦችን በማመንጨት ለከፍተኛ ተፋሰስ ምክር ቤት እስከ አሁን እንዲቀርብ የተደረገ ሃሳብ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

90. የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ ጥናቶች እየተጠኑ የፖሊሲ ሃሳቦችን ለማመንጨት የሚያግዙ ሃሳቦች ለተፋሰስ ከፍተኛ ምክር ቤት አለማቅረቡ፤ የወንዞች እና ረግረግማ መሬቶች ደህንነት፣ በውሃ አጠቃቀም፣ በተፋሰስ ልማት፣ በደን ልማት፣ በአካባቢ ብክለት እና በመሳሰሉት ዙርያ የወጡና እየተፈጸሙ ያሉ መመሪያዎች፣ ህጎች እና ፖሊሲዎች እንዳይዳብሩ እና የሚጠበቀውን ውጤት እንዳያስገኙ ያደርጋል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ፡-**

91. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ወሳኝ የሆኑ በቀጥታ የውሃ ሀብት አስተዳደር የሚመለከታቸው አካላት ጋር የተፋሰሱን ውሃ ሀብት ለማቀድና ለመወሰን የሚረዳ የቅንጅትና የትስስር ፎረም መመስረት፣ በጋራ ማቀድና የስራ አፈፃፀምን በጋራ መገምገም አለበት፡፡

92. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ የውሃ ሀብት አስተዳደር እና የተፋሰስ ልማት እንክብካቤ ሥራዎችን በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት (የክልል፣ የዞን እና ወረዳ መሬት አስተዳደር፣ የመስኖ ልማት፣ ኢንቨስትመንት ፣ ማዕድን እና ኢነርጂ ጽ/ቤቶች...) ጋር የተፋሰሱን የውሃ ሀብት ለማቀድ፣ ለመጠቀም፣ ለመንከባከብ እና ለመወሰን የሚረዳ የቅንጅትና የምክክር መድረክ የሌለው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ከወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

93. ስለ ጉዳዩ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ግንዛቤ ለመፍጠር በሚጠራው ስብሰባዎች ላይ የሚሳተፉት ሰዎች የተለያዩ በመሆናቸው ሥራን ሰጥቶ በዚሁ ልክ በመከታተል ተጠያቂ የሚደረግበትን ሁኔታ ለመፍጠር አለመቻሉን እና ከውሃ ተጠቃሚዎች ጋር

ፎረም ለመመስረት በአባያ ጫሞ ንዑስ ተፋሰስ የቅንጅትና የምክክር መድረክ የተዘጋጀ ሲሆን ይህን ተሞክሮ በሌሎች ተፋሰሶች ላይ ለማስፋፋት ያቀዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

94. በተፋሰሱ ውስጥ የቅንጅትና የትስስር ፎረም ባለመመስረቱ፤ አግባብ ባላቸው አካላት መካከል ውጤታማ የግንኙነት መድረክ እዳይፈጠር በማድረግ ወጥና ተከታታይነት ያለው የዕቅድ አፈፃፀም፣ ክትትልና የግምገማ ስርዓት እንዳይኖር እና የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲጠፋ ያደርጋል፡፡

## በተፋሰሱ ውስጥ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያስፈልጉ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች በቅንጅት መሰራታቸውን በተመለከተ፡-

95. በተፋሰሱ ውስጥ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያስፈልጉ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡ ቅንጅቱም ተፋሰሱ ከሚገኝባቸው እና የተጎዱ አካባቢዎች ከሚገኙ የወረዳ አካላት እና የውሃ ተጠቃሚዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡

96. በኦዲቱ ወቅት በህዋሳ እና ዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው ውሃ ተጠቃሚ ድርጅቶች ባሉበት አካባቢ በሀይቆችና በውሃ አካላት ዙሪያ የተጎዱ አካባቢዎችን ለማልማትና ለማንከባከብ ፍላጎት ያላቸው ቢሆንም የተጎዱ አካባቢዎች ያሉበትን ቦታ፣ የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና ማልማት የሚቻልበትን ሁኔታ በማመቻቸት የሚያስተባብር አካል ባለመኖሩ መስራት አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ባለስልጣን መ/ቤቱ የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ፕሮጀክት ቀርጾ የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን /physical structures/ ያከናወነባቸው ቦታዎች ላይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ሙሉ በሙሉ በሥነ ህይወታዊ /biological/ ሥራዎች በጋራ መሰራት ሲገባቸው ያልተሰሩ/ ያልተደገፉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በመስክ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

97. ስለ ሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በጥቁር ውሃ አካባቢ ከምርጥ ዘር ድርጅት ጋር አብሮ ለመስራት የተደረገ ሙከራ መኖሩን፣ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ለመስራት ያደረጉት ጥረት የሌለ መሆኑን እንዲሁም ለወደፊት ከነዚህ ድርጅቶች ጋር መስራት እንደሚጠበቅባቸው እና በኦዲቱ የተገለጸው ክፍተት ላይ ለወደፊት አቅደው የሚሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

98. በተፋሰሱ ውስጥ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያስፈልጉ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት አለመስራት የውሃ ተጠቃሚዎችና ከተፋሰሱ አካበቢ የሚኖሩ ህብረተሰብና አስተዳደሮች የሚገኘውን የገንዘብ፣ ጉልበት እና የተለያዩ ግዕባቶች እንዳይጠቀም ከማድረጉም በላይ የባለቤትነት ስሜት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በቅንጅት ባለመሰራቱ በተለያዩ አካላት የሚሰሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ቀጣይነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

**በባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፡-**

99. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡

100. ይሁን እንጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን (ወቅታዊ የሆነ የውሃ መጠንና ጥራትን፣ የወንዞች የፍሰት መጠን፣ የሀይቆች ከፍታና ዝቅታ መጠን፣ የወንዞች እና የሀይቆች የደለል መጠን፣ እንዲሁም የውሃ ተጠቃሚዎች አይነትና ብዛት) መረጃው የሌለ መሆኑ፣ በተለያዩ አካላት (በተማሪዎችና በተመራማሪዎች) ስለተፋሰሱ የተጠኑ ጥናቶችን የማይሰበሰቡና የማይተነተኑ መሆኑ፣ እንዲሁም ሌሎች ከተፋሰሱ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር እና በመተንተን መረጃዎችን አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የሚለዋወጥበትና የሚይዝበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት እንደሌለው ታውቋል፡፡

101. በተጨማሪም ባለሥልጣን መ/ቤቱ፡-

- በተፋሰሱ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት፣ ስነ-ህዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ሜትሮዋሎጂ፣ ሀይድሮሎጂ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ለመሰብሰብና ለማደራጀት የሚረዳ የመረጃ ቋት (Data Base) አለመኖሩን፣
- በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ የሐይድሮሎጂ ጣቢያዎችን ከውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ከሐምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ የተረከበ ቢሆንም ነገር ግን አብዛኛዎቹ መሳሪያዎች አገልግሎት የማይሰጡ፣ አስፈላጊው ጥገናም ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ያልተፈተሹ (calibration

Test) ያልተደረገላቸው በመሆኑ መረጃዎችን በተገቢው መልኩ መስጠት አለመቻላቸውን፣

- የሀይድሮሎጂ መሳሪያዎች አዲስ ተተክሎላቸው የተቋቋሙትም ጣቢያዎችና መሳሪያዎቹ ወደ አገልግሎት ያልገቡ እና የሀይድሮሎጂ ጣቢያዎች የሚሰበሰቡትን መረጃ በማዕከል ሆኖ ለማሰባሰብ የሚያግዝ ኔትዎርክ ያልተዘረጋላቸው መሆኑን፣
- በሻላ ንዑስ ተፋሰስ ዉስጥ የሚገኙ ወረዳዎች ሁሉም የመለኪያ ጣቢያዎች (hydrological stations) የሌሉባቸዉ አካባቢዎች መሆኑን እና በንዑስ ተፋሰሱ ዉስጥ ያለዉ የከርሰ ምድር ውሃ መጠን (ground water potential) የማይታወቅ መሆኑን እንዲሁም
- ካታር ወንዝ ከ25 በላይ ገባር ወንዞችና ጅረቶች ቢኖሩትም የወንዞቹን የፍሰት መጠን የሚለካበት የሐይድሮሎጂ ጣቢያዎች በወንዞቹ ላይ ባለመኖራቸው መረጃዎችን ማሰባሰብ አለመቻሉን

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

102. ስለ መረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓቱ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ መረጃ የሚለዋወጡበት የኤሌክትሮኒክ መገናኛ (ሊንክ) አለመኖሩን፣ በተፋሰሱ ውስጥ የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎች በተለይ የወንዞች ፍሰት መጠን ጋር ተያይዞ መረጃዎች እንደ መሳሪያው አይነት በየጊዜው /በየቀኑ/ የሚሰበሰቡ መሆኑን፣ ነገር ግን ዳታ ቤዝ ባለመኖሩ የሚሰበስቡትን መረጃዎች በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ የሚያዙ መሆኑ፣ ከውሃ ጥራት ጋር ተያይዞ የተሰራ ስራ አለመኖሩን፣ ከውሃ መጠን ጋር ተያይዞ በዚህ አመት ለመስራት ማቀዳቸውን እና እስከ አሁን መጠኑ እንዲለካ የተደረገ ሐይቅ አለመኖሩን እንዲሁም በተለያዩ አካላት የተጠኑ ጥናቶችን ከማሰባሰብ ጋር ተያይዞ በተለያዩ አማካሪዎች የተሰሩ ጥናቶችን ማግኘት አለመቻላቸውን፣ ብዙ የተደረጉ ጥናቶችን በማሰባሰብ ዙሪያ አለመስራታቸውንና ለወደፊት የሚሰሩበት መሆኑን እንዲሁም የመረጃ ቋት ለማቋቋም እቅድ የተያዘ ቢሆንም የባለሙያ እጥረት ስላለባቸው እስከ አሁን የተጀመረ ስራ አለመኖሩን ገልጸዋል ፡፡

103. በተፋሰሱ ውስጥ የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎች በማሰባሰብ፣ በማጠናከር ዘመናዊ የመረጃ

አያያዝ እና ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ አለመተግበሩ የተፋሰሱን የውሃ ሀብት አጠቃቀምና አስተዳደርን የሚመለከቱ መረጃዎች የተሳሳቱ እንዲሆኑ በማድረግ በተፋሰሱ ውስጥ የሚከናወኑ ሥራዎች ጥራት እና ዘላቂነት እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ ከሌሎች ከዘርፉ ዕውቀት ካላቸው አካላት ተጨማሪ ግብዓት እንዳይገኝያደርጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

104. የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ እና የውሃ ሀብት አስተዳደር አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን እና የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች በመኖሩ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

- በተፋሰሱ ውስጥ በሁለት ንዑስ ተፋሰሶች በናሙና ተመርጠው በታዩ በ8 ወረዳዎች በተለያየ ምክንያት ደኖች የሚጨፈጨፉ መሆኑ፣
- ለማረስና አመቺ ያልሆኑ ተራራማና ኮረብታማ ቦታዎች እንዲሁም ከዚህ ቀደም ያልታረሱ (በደን የተሸፈኑ፣ ወንዝ ዳር የሚገኙ ውሃ አዘል መሬቶች፣ እና የውሃ ምንጭ የሚፈልቅባቸው ቦታዎች) ወደ እርሻ መሬትነት የተቀየሩ መሆኑ፣
- ከተራራዎችና ከወንዞች አሸዋ የሚወጣ መሆኑ በውሃ አካላት ላይ ( የወንዞች ፍሰት መቀነስ እና በበጋ ወቅት ፍሰታቸው በመቋረጡ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በደለል እየተሟሉ ሀይቆች እያቀነሱ መሆኑ፣
- ስነ-ምህዳር /ecosystem/ ባለበት ሁኔታ መጠበቅ እና ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ያለው ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የተጎዱ አካባቢዎችን እንደጉዳት መጠናቸው ቅደሚያ በመስጠት ለማልማትና ለመንከባከብ ቦታዎቹን ለመመረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መምረጫ መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- ከፍተኛ ችግር ያለባቸው በጣም ገላጣ ፣ተራራማ/ከፍታማ፣ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ቦረቦሮች እና ገደላ ገደል የበዛባቸው ለአደጋ የተጋለጡ /የተጎዱ/ በመኖሩ በሚሊዮን ቶን የሚገመት ለም አፈር በጎርፍ እየታጠበ ወደ ወንዞችና ሐይቆች የሚገባ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ልማት ስራ ላይ ተሰማርተው ያሉ ልማት ድርጅቶችንና በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት በማሳተፍ /በማስተባበር/ ጉዳት ያለባቸው እና ውሃ

አካላት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አካባቢዎች ላይ የሚያስፈልገውን አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ያልሰራ መሆኑ፣

- በባለስልጣን መ/ቤቱ ድጋፍ የተሰሩ ስነ-አካላዊ ስራዎች የቴክኒካል ስታንዳርዱን ጠብቀው ያልተሰሩ እና የጥራት ችግር ያለባቸው በመሆኑ፤ አገልግሎት መስጠት እንደጀመሩ እየፈራረሱሱ መሆኑ፣ የተሰራው የክትር (ጋቢዎን) ስራ የጎርፍ ግፊት መጠን /discharge rate/ ያልተጠና እና ርቀታቸውን /interval/ ጠብቆ አለመሰራታቸው፣ በተሰራው ክትር/ ጋቢዎን አልፎ የሚፈስ ውሃ የሚያርፍበት ቦታ /Apron/ ያልተሰራለት በመሆኑ ተጨማሪ የመሬት መቦርቦር እያስከተለ መሆኑ፣
- እንዲሁም የተሰሩ የስነ-አካላዊ (physical) ስራዎችን በስነ-ሕይወታዊ (Biological) ስራዎች አለመደገፋቸው፣
- ችግኝ ተከላ የተደረገባቸው ቦታዎች አጥር/ጥበቃ የሌላቸው መሆኑና አብዛኞቹ ያልጸደቁ መሆናቸው፣
- በአርሶ አደሩ ተሳትፎ የተከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በየዓመቱ በእርሻ ምክንያት የሚበላሹበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ሀይቆቹ ዙሪያ ያለውን ህብረተሰብ ከሀይቁ ጥገኝነት ለማላቀቅ ሲባል የሚከናወኑ የስራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች ለሚመለከታቸው ሰዎች ያልተሰጠ /ለታለመለት ዓላማ አለመዋሉ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በከፍተኛ ወጪ እና በህብረተሰቡ የጉልበት ተሳትፎ የተሰሩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ቀጣይነት ለማስጠበቅና የተቀረጸውን የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ፕሮጀክት ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ፈጻሚዎች ጋር በመሆን የማይከታተልና የማይገመግም መሆኑ፣
- በተፋሰሱ በሀይቆችና ወንዞች ላይ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮዊ ችግሮች የሚደርሱትን ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል የውሃ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚረዳ መመሪያ ወይም የትግበራ ማንዋል ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

- ባለስልጣኑ በተፋሰሱ በሀይቆችና ውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ልማት ፕሮጀክቶች በሚያደርጉት የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ አስተያይት የማይሰጥና በጥናቱ መሰረት መተግበራቸውንም የማይከታተል መሆኑ፣
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በየአካባቢያቸው ለተፋሰሱ የባለቤትነት ስሜትን ለመፍጠር የሚያስችል ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ያልሰራ መሆኑ፣
- በሐይቆችና በረግረጋማ መሬቶች አካባቢ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት ላይ ክትትል በማደረግ በሚፈጠሩ ችግሮችና ጥሰቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረጉ፣
- በባለስልጣኑ በጀት ድጋፍ የሚከናወኑ የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣
- በውሃ ተጠቃሚዎች መካከል የአጠቃቀም ግጭቶችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚስችል ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ አጠቃላይ በተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ተጠቃሚዎች ብዛት እና የሚጠቀሙትን የውሃ መጠን ለይቶ የማያውቅ መሆኑ፣
- በውሃ ክፍያ ላይ የአከፋፈል ታሪፍ የሌለና፣ በተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ የውሃ ሀብት የሚጠቀሙ ድርጅቶች ለሚጠቀሙት ውሃ የሚከፍሉት ክፍያ የሌለ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ መደበኛ ሂደታቸውን እንዳይቀይሩ ክትትል የማያደርግ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ እና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያግዙ ሃሳቦችን ለማመንጨት የሚረዱ ጥናቶችን በማከናወን እና ትንትና በመስራት የፖሊሲ መነሻ ሃሰቦችን ለከፍተኛ ተፋሰስ ምክር ቤት ያለቀረበ መሆኑ፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ የውሃ ሀብት አስተዳደር እና የተፋሰስ ልማት እንክብካቤ ሥራዎችን በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት (የክልል፣ የዞን እና ወረዳ መሬት አስተዳደር፣ የመስኖ ልማት፣ ኢንቨስትመንት ፣ ማዕድን እና ኢነርጂ ጽ/ቤቶች...) ጋር የተፋሰሱን የውሃ ሀብት ለማቀድ ለመጠቀም፣ ለመንከባከብ እና ለመወሰን የሚረዳ የቅንጅትና የምክክር መድረክ የሌለው መሆኑ፣

- በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችና ጥናቶቹን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር እና በመተንተን መረጃዎችን አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የሚለዋወጥበትና የሚይዝበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣
- በተፋሰሱ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት፣ ስነ-ህዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ሜትሮዋሎጂ፣ ሀይድሮሎጂ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ለመሰብሰብና ለማደራጀት የሚረዳ የመረጃ ቋት (Data Base) አለመኖሩ፣
- በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ የሐይድሮሎጂ ጣቢያዎችን አብዛኛዎቹ መሳሪያዎች አገልግሎት የማይሰጡ፣ አስፈላጊው ጥገናም ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ያልተፈተሹ (clibration Test) ያልተደረገላቸው እንዲሁም የኃይድሮሊክ ጣቢዎች ያልተቋቋመባቸው ገባር ወንዞች መኖራቸው፣

ታውቋል፡፡

105. ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች እና ግድፈቶች በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የተቀናጀ ሁሉን አቀፍ የውሃ ሀብት አስተዳደር እና ዘላቂ የአከባቢ ልማትና እንክብካቤ ሥርዓትን ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

106. የውሃ ሀብት አስተዳደር እና ዘላቂ የአከባቢ ልማትና እንክብካቤ ሥርዓትን ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የተጎዳን መሬት መልሶ ለማልማትና ስነ-ምህዳርን ከውድመት ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ በተመረጡ ስፍራዎች የተከለለ መሬትን ከሰውና ከእንስሳ ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ፣ በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች ከፍተኛ የአካባቢ መራቆት የሚታይባቸውን በጥቃቅን ተፋሰስ (micro watershed) በመለየትና በደረጃ ሊያስቀምጥ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡
- የተለያዩ ልማት ሥራዎች ሲከናወኑ የተፋሰሱን ስነምህዳር ለመጠበቅና ጉዳቶችን ለመከላከል ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመሆን የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ጋር ተያይዞ ያሉ የመንግስት ፖሊሲዎችን ባማከለ መልኩ በማንኛውም ልማት ድርጅት ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ወጥ የሆነ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ሐይቆች እና ወንዞች ያለባቸውን የስህነምዳር እና የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታ በማጥናት እና በጥናቱ መሰረት እየደረሰባቸው የሚገኘውን ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችል የመፍትሄ እርምጃ መውሰድና የተጀመሩ ሥራዎችን በመደገፍ ማጠናከር አለበት፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር በመመካከር እና በመተባበር የተፋሰሱ የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ወሰን (Buffer Zones) የሚከለልበት የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት እና ለከፍተኛው የተፋሰስ ምክር ቤት አቅርቦ እንዲጸድቅ በማድረግ በተከለሉ የውሃ አካላት ዳርቻዎች ክልል ውስጥ ያሉ እጽዋት ሽፋኖች ወይም ዛፎች እንዳይመነጠሩ ወይም እንዳይቆረጡ፣ የመኖሪያ ቤቶች እንዳይገነቡ፣እና ሌሎች ዳርቻዎቹን የሚጎዱ ተግባራት እንዳከናወኑ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በሀይቆች አካባቢ የሚገኙ ረግረጋማ መሬቶች እንዳይታረሱ እንዲከለል ሊያደርግ፣ (delineation of the wetlands)፣ ለባለድርሻ አካላትና በተፋሰሱ ውስጥ ለሚኖረው ህበረተሰብ በተፋሰሱ ልማትና እንክብካቤ ዙሪያ  በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሀይቆችን ለማስተዳደር እና ለመንከባከብ የሚያስችል የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ፕሮጀክትን በሁሉም ሐይቆች ዙሪያ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ወጥና በጥናት ላይ የተመሰረተ ሳይንሳዊ መምረጫ መስፈርት በማውጣት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት የፕሮጀክት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተፋሰስ በመለየት የፕሮጀክት ዶክመንት ማዘጋጀት፣ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸትና ስነ አካላዊ እና የስነ- ህይወታዊ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራን እንደ አስፈላጊነቱ የአፈር ካብ፣ የጋቢዮን ክትር፣ የድንጋይ ክትር፣ የእንጨት ክትር፣ ማይክሮ ቤዝን፣ ውሃ ማስረጊያ ጉድጓድ፣ የህብረተሰብ ኩሬ እና የቤተሰብ ገንዳ፣ ችግኝ ጣቢያዎችን የማስተካከል ሥራ፣ የተለያዩ የችግኝ ዝርያዎችን የማፍላት፣ የችግኞችን ጉድጓድ አዘጋጅቶ መትከልና በማንከባከብ  የተፋሰሱን የተፈጥሮ ሃብት ልማትና እንክብካቤ ሥራችን በማከናወን በመራቆት ላይ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት መልሶ እንዲያገግም በማድረግ አርሶ አደሩ የሚጠቀማቸው ማዳበሪያና ሌሎች ኬሚካሎች በዝናብና ጎርፍ ታጥበው ወደ ውሃ አካላት እንዳይገቡ እና የደለል መጠን እንዲቀንስ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ በሀይቆችና ወንዞች ላይ በተለያዩ ሰው ሰራሽና  ተፈጥሮአዊ ችግሮች የሚደርሱትን ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል የውሃ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚረዳ መመሪያ ወይም የትግበራ ማንዋል በማዘጋጀት በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡  ማንዋሉም ለሚመለከተው አካል ወይም ለፕሮጀክት ፈጻሚ አካል ማሰራጨትና በተፋሰሱ ውስጥ ስነ አካላዊ እና ስነ-ህይወታዊ ስራዎችን በማንዋሉ መሰረት በትክክል መከናወናቸውን በመከታተል መገምገም ይኖርበታል፡፡
- ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ጋር በመሆን የስነ-ሕይወታዊና ስነ- አካላዊ ስራዎች ሲከናወኑ በአብዛኛው ሥራ በህብረተሰቡ ጉልበት ተሳትፎ የሚሰራ በመሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል በማደረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በወቅቱ በመልቀቅ እና

ከወረዳዎቹ ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በተፋሰሱ ውስጥ ውሃ የሚጠቀሙ አካላት በሙሉ የውሃ ሀብት ለመጠቀምና ውሃ ነክ ስራዎችን ለመራት የሚያስችል ፍቃድ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ በውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ 197/2000 እና ስለውሃ ሀብት አስተዳደር የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 115/2005 ዓ.ም መሰረት
  - ➢ ፈቃድ በመውሰድ እንዲሰሩ ሊደረግ እና ፈቃድ ያላወጡ አካላት ከውሃ መጠቀም እንዳይችሉ የሚያደረግበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
  - ➢ በተጨማሪም ማናቸውም ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎችን የባለሥልጣኑን ፈቃድ ሳያገኙ ማናቸውም አካላት በተፋሰሱ ሥር ወደሚገኙ የውሃ አካላት ለመልቀቅ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ መውሰዳቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፤ የሚለቀቀውም ፍሳሽ ታክሞ ስለመለቀቁ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በየጊዜው የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
  - ➢ ካለፈቃድ ውሃ የሚጠቀም እና ሳይታከም ቆሻሻዎችን ወደ ውሃ አካላት በሚለቁ ማናቸውም አካላት ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እና የህግ እርምጃ ባለሥልጣኑ ሊወስድ ይገባል፡፡
- የመስኖ አጠቃቀሙን ዘመናዊ ማድረግ (Drip and sprinkler irrigation syatems)፣ የሐይቁን ዙሪያ በመከለልና ኬሚካልን በሚቋቋሙ ዕጽዋቶችን በማልማት ጎርፉንና ብክለቱን መከላከል እና የውሃ ሀብት እንዳይበከል እና ለጤናና ለአካባቢ የጤና ጠንቅ አለመሆኑን ለማረጋገጥ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመመካከር በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ ሀይቆችንና ብዝሀ ህይወቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በመለየት፣ ሀይቆችና ላይ በሚፈጥሩት ተፅዕኖ መሰረት ችግሮቹን መቅረፍ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ሀይቆችና ብዝሀ ህይወቱ ላይ የሚፈጠረውን ተጽዕኖ መቀነስና መከላከል ይኖርበታል፡፡
- የውሃ ሀብትን ለማልማትና ህዝቡን የልማቱ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ፈቃዶች አካባቢንና ህዝብን ማዕከል ያደረጉ ጉዳዮችን በጥንቃቄ በመመርመር እና የሚመለከታቸውን አካላትን እና ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተሳተፈበት መሆን አለበት፡፡ ፈቃዱ የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት ስራዎችም

ፍቃድ በወሰዱት መሰረት መተግበራቸውን ባለሥልጣኑ ሊቆጣጠርና ተገቢውን የቴክንክ ድጋፍ ሊያደረግ ይገባል፡፡


- ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ተግባር እድሸጋገሩ፤ ባለሥልጣኑ በጀትን በወቅቱ ሊለቅና አስፈላጊ በሆኑ ኮዶች ላይ ሊመደብ፣ ፕሮጀክቶቹ ያሉባቸው ወረዳዎች መረጃና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን በየጊዜው እንዲቀርብ ሊያደርግ፣ ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጀመሩ ሊያደረግ፣ የፕሮጀክቱን ተግባራት የሚያከነውኑ አካላቶች በገቡት ውል መሰረት የፕሮጀክት ስራዎችን አጠናቀው እንዲያስረክቡ ክትትል ሊያደርግ እና የድንጋይና ጋብዮንም ሆነ የሌላ ቁሳቁሶች ግዥዎች በወቅቱ ሊፈጸም ይገባል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ሀብት በተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳዳር ስር በማዋል የተፋሰሱን ስነ- ምህዳር የጠበቀ፣ ዘላቂና ፍትሐዊ እንዲሁም ከብክለት ነፃ የሆነ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የውሃ መጠንን ማወቅና መለየት እንዲሁም በተገኘው የውሃ አቅም ጥናት ውጤት /የተፋሰሱን ውሃ ፍላጎትና ያለው ውሃ መጠን ባገናዘበ መልኩ/ መሰረት ፍትሃዊ የውሃ ምደባ ሊያካሂድ፣ የውሃ ተጠቃሚዎችን በመለየት ፈቃድ እንዲያወጡ ሊያደርግ፣ በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ለማስቀረት ለመፍታት የሚረዳ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣኑ በተፋሰሱ ውሃ ተጠቃሚዎች ለሚጠቀሙት ውሃ መጠን ክፍያ እንዲከፍሉ የሚያስችል ታሪፍ የሚወሰንበት የሕግ ማዕቀፍ እና ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ያሉ የወንዞችን ፍሰት ሁኔታ በመከታተል በክረምት ወቅት አቅጣጫቸውን ስተው ጉዳት በማህበረሰቡ ላይ እዳያደርሱ በቅድሚያ ከሚመለከታቸው የክልልና ወረዳ አካላት ጋር በመቀናጀት ስነ- አካላዊ እና የስነ- ህይወታዊ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣኑ በተፋሰስ ደረጃ የአየር ሁኔታን እና የተፋሰሱን ዓመታዊና ወቅታዊ የዝናብ መጠንና ስርጭት በመለየት ለዓመታዊ የወንዝ ፍሰት ያለውን አስተዋፅዎ በመተንተን፣ ተፈጥሮአዊ የወንዞች ፍሰትን የሚያስተጓጉሉ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ችግሮችን ሊከታተልና የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የስምጥ ሸለቆ ሃይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን ለከፍተኛ የተፋሰስ ምክር ቤት ሁሉንም የውሃ አካላት ከጉዳት ለመከላከል በህግም በፖሊሲ ደረጃም ምክረ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣንና ተግባር የተሰጠው ሲሆን በዚህ ደረጃ በሃይቆች፣ ወንዞች እና ረግረግማ መሬቶች ደህንነት፣ በውሃ አጠቃቀም፣ በተፋሰስ ልማት፣ በደን ልማት፣ በአካባቢ ብክለት እና በመሳሰሉት ጋር ተያይዘው የወጡና እየተፈጸሙ ያሉ መመሪያዎች፣ ህጎች እና ፖሊሲዎች አቀራረጽና አፈጻጸማቸው በመፈተሽ የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ሀሳቦችን በማመንጨት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ አለበት፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውሃ ሀብት ጋር ቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው አካላት ጋር የቅንጅትና የትስስር ፎረም በመመስረት ስለ ውሃ ሀብት መረጃ መለዋወጥ፣ መመካከር፣ ማቀድና መወሰን፤ ሁሉንም አጋር አካላት የሚያሳትፍ የተቀናጀ ስራን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ፤ ወጥና ተከታታይነት ያለው የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና የግምገማ ስርዓት መዘርጋት፤ የእቅድ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ማስፈጸሚያ ስልት መቅረጽ እንዲሁም ግልጽና አሳታፊ የሆነ የእቅድ ክትትልና ግምገማ ስርዓትን መተግበር አለበት፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይጠበቅበታል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውሃ ተጠቃሚዎችን በመለየት በየዓመቱ የሚጠቀሙትን ውሃ መጠን መረጃ መያዝ፤ በተፋሰሱ ዙሪያ በተለያዩ አካላት የተጠኑ ጥናቶች በማሰባሰብ ሊይዝ ፣ በጥናቶቹ ላይ የተቀመጡ መፍትሄ ሃሳቦችን ተግባራዊ ሊያደረግ፣ በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ኃብት በተለይ ውሃ ሀብት፣ ስነ-ህዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ሜቲሮሎጂ፣ ሀይድሮሎጂ እና የመሳሰሉትን መረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማደራጀት የሚረዳ መረጃ ቋት ሊያቋቁም ይገባል፡፡
- ባለሥልጣኑ ከዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር በመሆን በተፋሰሱ እየታዩ ያሉ ችግሮችን በቅደም ተከተል የመለየትና መፍትሄ የማስቀመጥ ተግባራትን ማከናወን፣ የምርምር ስራዎችን አጠናክሮ ለመቀጠል የላቦራቶሪ ማዕከላትን ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ደርጅቶች ጋር በመሆን የማደራጀት፣ የሃይቆቹን ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ባህላዊ እና ስነ- ህይወታዊ ጠቀሜታዎችን በማጉላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰራዎች ለመስራት እና

ለደህንነታቸው ስጋት የሆኑትን ነባራዊ ችግሮች ለማወቅ በተለያየ መልኩ ጥልቅ የሆነ ጥናት (Research) ሊደረግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ መረጃ የተሰበሰበባቸውና የመስክ ጉብኝት የተደረገባቸው በናሙና የታዩ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ እንዲሁም ድርጅቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1: የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን መዋቅር



# አባሪ- 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች |
|---|---|
| 1. በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች ላይ የምደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ልማትና እንክብካቤ ተግባራት የተከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ | 2. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ ያሉ ስነ-ምህዳርን ከውድመት ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 3. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ውስጥ የሚገኙ የተፋሰሱ አከባቢዎች ያሉበትን ሁኔታ ሊያጠና ይገባል፡፡ |
| | 4. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ በጥናቱ መሰረት ጉዳት የደረሰባቸውን አከባቢዎች (የአፈር መሸርሸር፣ የእፅዋት መመናመን፣ የተራቆቱና በመራቆት ላይ ያሉ) መስፈርት በማውጣት መለየት ይኖርበታል፡፡ |
| | 5. በተፋሰሱ ውስጥ የተጎዱ አካባቢዎችን የሚያስፈልጉ አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊሰሩ ይገባል፡፡ |
| | 6. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የተቀናጀና ቀጣይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ሥራዎችን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሊገመግም ይገባል፡፡ |
| | 7. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ የውሃ ሀብት ልማትና ብዝሀ ህይወትን ለማስተዳደር የሚረዳ የአፈርና ውሃ ጥበቃ መመሪያ /Guideline/ በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል ሊያጸድቅ ይገባል፡፡ |
| | 8. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ የውሃ ሀብት ልማትና ብዝሀ ህይወትን ለማስተዳደር የሚረዳ የአፈርና ውሃ ጥበቃ መመሪያ/Guideline/ ለሚመለከታቸው አካላት በማሰራጨት ተግባራዊነቱን በየጊዜው ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 9. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሀይቆቹንና የብዝሀ ህይወቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ አሉታዊ ተጽኖዎችን የመለየት፣ የመቀነስና የመከላከል ስራን ከባለ ደርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 10. በተፋሰሱ፣ በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች የሚያከናውኑዋቸውን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ለይ ባለስልጣን መ/ቤቱ አስተያየት ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 11. ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ ሲደረጉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሰጣቸው አስተያየቶች ስለመተግበራቸው ክትትል ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12. በተፋሰሱ ለረግረጋማ መሬት አስተዳደር እና ለሃይቆች ዳርቻ ክልል አጠቃቀም የተሟላ የፖሊሲ ማእቀፍ እንዲሁም ደንብና መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 13. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ የረግረጋማ መሬት አስተዳደርና የሀይቆች ዳርቻ ክልልን በሚመለከት ጥናት ሊያካሄድ ይገባል፡፡ |
| | 14. በጥናቱ መሰረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የሀይቆች ዳርቻ ክልል( Buffer Zone) እና የረግረጋማ መሬት ወሰን የሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት እና በማጸደቅ ተግባራዊ |

| | |
|---|---|
| | ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 15. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በተፋሰሱ ረግረጋማ መሬቶች እንዳይታረሱ ለአርሶ አደሩ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራትና በሓይቆችና በረግረጋማ መሬቶች አከባቢ በሚካሄደው እንቨስትመንት ላይ ክትትል ማደረግ አለበት፡፡ |
| | 16. ከተሞችና እንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን አካባቢውን በማይጎዳ መልኩ መዘጋጀትና ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ወንዞች ከመለቀቃቸው በፊት ቆሻሻው መታከሙ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 17. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የጨዋማነት ደረጃን ለማወቅና ጨዋማነትን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት ማካሄድ እና የጥናቱን ውጤት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 18. የአሳ ሃብት ባለባቸው ሐይቆች ስርዓት ያለው የአሳ አሰጋገርና ተረፈ ምርት አወጋገድ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 19. ሁሉም የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው ወደ ተግባር ሊሸጋገሩ ይገባል፡፡ |
| | 20. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሐይድሮሎጂ ጣቢያዎችን መረከብ፣ ማጠናከር፣ ማቋቋም እና የሀይድሮሎጂ ጣቢያዎችን ኔትዎርክ መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ |
| **2. በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሂደት ፍታዊና አሳታፍ በሆነ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡፡** | 3. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የውሃ ምደባንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 4. ለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የሚካሄደውን ውሃ አጠቃቀምን (መስኖ፣ ፋብሪካዎች...) መጠን እና ክፍያ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 5. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ የውሃ አጠቃቀምና ውሃ ነክ ስራዎች ለመስራት የሚያስችል የፈቃድ ዓሰጣጥና እድሳት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 6. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ በውሃ ለመጠቀምና ውሃ ነክ ሥራዎች ፍቃድ የወሰዱ አካላት በፈቃዱ መሰረት እያከናወኑ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 7. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የውሃ አጠቃቀም ክፍያ ስርዓት በመዘርጋት ወይም መመሪያ በማዘጋጀት ከተጠቃሚዎች የውሃ ክፍያ መሰብሰብ አለበት፡፡ |
| | 8. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የወንዞችን የፍሰት ሁኔታ መከታተልና መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡ |
| **3. በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ መረጃዎችን ለመጠቀምና ለሚፈልገው ተገልጋይ በብቃት እና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል** | 9. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚረዱ የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨት ለምክር ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡ |
| | 10. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ወሳኝ የሆኑ በቀጥታ የውሃ ሀብት አስተዳደር የሚመለከታቸው አካላት ጋር የተፋሰሱን ውሃ ሀብት ለማቀድ፣ እና ለመወሰን የሚረዳ የቅንጅትና የትስስር ፎረም መመስረት፣ በጋራ ማቀድና የስራ አፈፃፀምን በጋራ መገምገም |

| | |
|---|---|
| እንዲሁም ቅንጅታዊ የአሰራር ስረዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤<br><br>3.1 በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ ቅንጅታዊ የአሰራር ስረዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፡፡ | አለበት፡፡ |
| | 11. በተፋሰሱ ውስጥ ለሚገኙ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር እና የውሃ ሀብት አጠቃቀምን በሚመለከት ግንዛቤ ሊፈጥር ይገባል፡፡ |
| | 12. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር በመሆን በተፋሰሱ ውስጥ ተግባሮቹን ለማከናወን የሚረዱ እና ውሃ ሀብት ላይ የታዩ ችግሮችን በመለየት ጥናቶችንና ምርምሮችን ሊያካሂድ እና ውጤቱን ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 13. ባለስልጣን መ/ቤቱ ተፋሰሱን የሚመለከቱ መረጃዎች አግባብ ካላቸው የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የሚለዋወጥበትና የሚይዝበት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 3.2 በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ውስጥ መረጃዎችን ለመጠቀምና ለሚፈልገው ተገልጋይ በብቃት እና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፡፡ | 14. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ የሚገኘውን የውሃ ሀብት በተገቢው ሁኔታ ለማቀድ፣ ለማስተዳደርና ለማንቀሳቀስ የሚጠቅሙ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡ |
| | 15. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ዋና ዋና የውሃ ተጠቃሚዎችን በመለየት በዓመት በአማካኝ የሚጠቀሙትን የውሃ መጠን በማወቅ መረጃውን አጠናክሮ መያዝ ይኖርበታል፡፡ |
| | 16. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች የሚገኙበትን ሁኔታ ላይ በተለያዩ አካላት የተጠኑ ጥናቶችን መረጃ በማሰባሰብ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 17. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ የተፈጥሮ ኃብት፣ ስነ-ህዝብ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ሜቲሮሎጂ፣ ሀይድሮሎጂ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ለመሰብሰብና ለማደራጀት የሚረዳ የመረጃ ቋት መመሰረት አለበት፡፡ |

## አባሪ 3: በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸውአካላት እና መስክ ምልከታ የተደረገባቸው አከባቢዎች ዝርዝር ማሳያ፡-

| ተ/ቁ | የንዑስ ተፋሰስ ስም | በናሙና የተመረጡ ወረዳ ግ/ጽ/ቤቶች | በናሙና የተመረጡ የገጠር ቀበሌዎች | በተመረጡ ቀበሌዎች የታዩ ሐይቆች፣ ወንዞችና ረግረጋማ መሬቶች | በንዑስ ተፋሰሱ መጠይቅ የቀረበላቸው ውሃ ተጠቃሚ ድርጅቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ | ቱላ ክፍለ ከተማ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - ቱሎ ቀበሌ<br>- ፍንጫዋ ቀበሌ<br>- ገመጦ ቀበሌ<br>- ሀቤላ ወንዶ ቀበሌ | - ሀዋሳ ሐይቅ | - ቢጂአይ የሀዋሳ ቢራ ፋብሪካ<br>- ኢታብ ሳሙና ፋብሪካ<br>- ሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብርካ<br>- ሞሃ ለስላሳ ፋብሪካ |
| | | ወንዶ ገነት ወረዳ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - ወሻ ሶያማ ቀበሌ<br>- ጩኮ ቀበሌ<br>- ኤዶ ቀበሌ<br>- ዩዎ ቀበሌ | - የፌል ውሃ ምንጭ | |
| | | ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - ላቡ ኮሮሞ ቀበሌ<br>- ጋሎ አርጌሳ ቀበሌ<br>- ኤዶ ወጣጤ ቀበሌ<br>- ሣማ ኤጀርሳ ቀበሌ | - ሀዋሳ ሀይቅ | |
| 2 | ዝዋይ-ሻላ ንዑስ ተፋሰስ | ጥዮ ወረዳ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - ዶሻ ቀበሌ<br>- ጫፌ ሚሶማ ቀበሌ | - ዶሻ ምንጭ ውሃ<br>- ጫፌ ሚሶማ ረግረጋማ መሬት | - ኤልፎራ አግሮ ኢንዱስትሪ /ኃ/የተ/የግል/ማ<br>- ለሼር ኢትዮጵያ ኃላ/የተ/የግል/ማለካስትል ዋይነሪ ኃላ/የተ/የግል/ማሰገን እርሻ ልማት ድርጅት<br>- ለሰላም የተፈጥሮ የታሸገ የማዕድን ውሃ የፋብርካ |
| | | ዝዋይ ዱግዳ ወረዳ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - ሄሬራ ቀበሌ<br>- በሺራ ጫፋ ቀበሌ<br>- ጫፌ ቡርቂቱ ቀበሌ<br>- አራጣ ቀበሌ | - ዝዋይ ሀይቅ<br>- ካታር ወንዝ<br>- ጩፋ ወንዝ<br>- ሼተ-ማታ፣ ጥኖ፣ ወንበራ፣ ገኖ፣ ወንበራ፣ ዋራቤ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ረግረጋማ መሬቶች | |
| | | ዱግዳ ቦራ ወረዳ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - ኦዳ ቦቆታ ቀበሌ | - መቂ ወንዝ | |
| | | አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - አብኔ ጋርማማ ቀበሌ<br>- ባቱ ከተማ | - ዝዋይ ሐይቅ<br>- ቡልቡላ ወንዝ | |
| | | አርሲ ነገሌ ወረዳ እርሻና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት | - ሃዳ ቦሶ ቀበሌ<br>- ቃራሩ ቀበሌ<br>- ጉርቢ አርባ<br>- ሻላ ቢላ ቀበሌ | - ላንጋኖ ሐይቅ<br>- አብጃታ ሐይቅ<br>- ሻላ ሀይቅ<br>- ሻላ ፊል ውሃ ምንጭ | |

Office of the Federal Auditor General